# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ



6ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የስድስተኛ ክፍል
# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ


ጸሐፊያን፡- ጥበቡ ወልደዮሐንስ
ይርጋ ቁምላቸው
ዮሐንስ ሰብስቤ

ገምጋሚዎች፡- እየሩሳሌም በዳኔ
ማርቆስ ወልደሃና
ሰሎሞን ኃይለማርያም

አስተባባሪ:-ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

ግራፊክ ዲዛይን፡- እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

© የመጽሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው ።

::

# ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽኃፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽኃፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና  የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

## ማውጫ


ርዕስ ገፅ

የመጽሐፉ መግቢያ. ........ IV

ምዕራፍ አንድ፡- ጥበባዊ ግንዛቤ ........ 1

መግቢያ. ........ 1

1.1 የሜጀርና የማይነር ስኬሎች ክረቶችና የቁልፍ ምልክቶች (Key signatures) ........ 1

1.1.1. የዲያቶኒክ ሜጀር ስኬል ........ 2

1.1.2 የዲያቶኒክ ማይነር ስኬል. ........ 3

1.1.3 የቁልፍ ምልክቶች (Key signatures). ........ 5

1.2. ውዝዋዜ (አካል እንቅስቃሴ ጅማሮ) ........ 9

1.3. የቲያትር ጥበባት (ድርጊት፣ መምራት፣ ጨዋታ መፃፍና፣ የፊልም ጥበባት ........ 11

1.3.1 ድርሰት. ........ 12

1.3.2 የትያትር አላባውያን መሰረቶች. ........ 12

1.3.3. የተውኔት ዘውጎች (ቴክኒካዊ). ........ 14

1.3.4. የተውኔት አዘገጃጀት. ........ 16

1.4. ቀለም ቅብና ሌሎች የዕይታ ጥበባት. ........ 18

1.4.1.ንድፍ /ዲዛይን/. ........ 19

ምዕራፍ ሁለት፡- ፈጠራን መግለጽ ........ 25

መግቢያ ........ 25

2.1 ስልተምት ከሆሄያት ጋር መቁጠር ........ 26

2.1.1 የተጻፉትን ምቶች በመቁጠር ተለማመዱ. ........ 27

2.1.2. በትሬብል ክሌፍና በቤዝ ክሌፍ ስታፍ ላይ የተፃፉ ኖቶችን ማንበብ. ........ 29

2.1.3. የቀጭንና የወፍራም ድምፅ ክረቶች. ........ 30

2.2. በውዝዋዜ ስልተ ምትን መረዳት ........ 31

2.3. በቲያትር በቪዱዮና በፍቶ ግራፍ ሃሳቦችን መግለፅ ........ 32

2.3.1. ንግግር አልባ ትወናዎች. ........ 32

2.3.2 ድንገቴ ፈጠራ. ........ 34

2.4.ንድፍለቀለምቅብናለህትመት ........ 35

2.4.1 የርቀትና ቅርበት / ዕርዮተአድማስ /. ........ 37

2.4.2 ርቀትና ቅርበት ብርሃንና ጥላ. ........ 38

ምዕራፍ ሶስት፡- ታሪካዊና ባህላዊ አግባብ/አውድ/ ..... 42
የተፃፉ ታሪኮችን. ..... 42
መግቢያ ..... 42
3.1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ..... 43
3.1.1. የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች ..... 43
3.1.2 የትንፋሽ መሳሪያዎች. ..... 46
3.1.3 የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች. ..... 50
3.1.4 በእጅ በማንቃነቅና በጣት በመምታት ድምፅ የሚያወጡ መሳሪያዎች. ..... 52
3.2.የሀገረሰብውዜዋዜዎች ..... 54
3.3ታሪክእንዴትይተረካል ..... 55
3.4 የተጻፈ ታሪኮችን በዕይታ ጥበባት ማብራራት ..... 63
ምዕራፍ አራት ፡- ሥነ ውበታዊ ጥቅም (ዋጋ) ..... 69
መግቢያ. ..... 69
4.1 አገር በቀል እውቀቶች በሙዚቃ ጥበብ ማድነቅ ..... 70
4.1.1 የዜማ ክዋኔዎች. ..... 70
4.2 ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በውዝዋዜ ማድነቅ ..... 71
4.3. የትውፊታዊ ተውኔት ምንነት ..... 72
4.3.1. የትውፊታዊ ተውኔት ባህርያትና ክዋኔዎች. ..... 73
4.4 የሀገር በቀል ዕውቀቶች በዕይታ ጥባባት ማድነቅ ..... 74
ምዕራፍ አምስት፡-ጥመርታ ዝምድናናትግበራ ..... 80
ክወናና ዕይታ ጥበብን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር ..... 80
5.1 ጥበባትን ከአካባቢ እንክብካቤ ጥበቃ ጋርና ከሀገር ሀብት ጋር ማቆራኘት ..... 80
5.1.1 አካባቢ ብክልት. ..... 80
5.1.2 የአካባቢ እንክብካቤ. ..... 81
5.2 የክወና ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶችና ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የስርዓተ ፆታ የትራፊክ፤ጤና ወዘተ ጋር ማገናኘ ..... 81
5.2.1 የሙዚቃ ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር. ..... 82
5.2.2 ውዝዋዜ ከትምህርቶች ጋር ማጣመር ..... 83
5.2.3. ተግባራዊ ክዋኔን ማሳየት. ..... 84
5.2.4. የዕይታ ጥበብ ከሌሎች የት/ት አይነቶችጋር ያልው ጥምርታ. ..... 89

# የመጽሐፉ መግቢያ:-

በዚህ ክፍል ስለ እይታዊና ክዋኔያዊ ጥበባት ማለትም ስለ ሙዚቃ ተፈጥሮ፣ የሙዚቃ ጥበብ አሰራር፣ የውዝዋዜ ምንነትና ዓይነቶች፣ ስለ ትያትር ተፈጥሮ፣ ትወና፣ ዝግጅት፣ ቃለተውኔትና ቪዲዮ (ፊልም) ጥበባት እንዲሁም ሀገር በቀል እውቀቶችን በጥበባዊ ዘዴዎች በማጣመር፤ እና የስዕል ተፈጥሯዊ ምንነትና አሰራር መወቅራዊ ሂደቱን በጠበቀ መልኩ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች እነዚህን ጥበባት ከተማራችሁ በኋላ ለእይታዊና ክዋኔያዊ ጥበባት የቀረቡ ስራወችንና መልመጃወችን በተገቢ ሁኔታ በመመለስና በትግበራዎች ላይ በመሳተፍ ክህሎታችሁን በእውቀት እንድታበለፅጉ ታስቦ የተዘጋጀ መፅሐፍ ነው፡፡

ይህ የስድስተኛ ክፍል መጽሐፍ የሚያተኩረው ስኬል ተከታታይነት ያላቸው ድምፆች እርቀት ምልክቶች ናቸው ስኬል ለሙዚቃ ዜማ ድርሰት ዋናው የሙዚቃ ክፍሎች አንዱ የድምፆች አደራደር ስነጥበባዊ ቅንብር ውጤት ነው፡፡

ውዝዋዜ ወይም ዳንስ የስው ልጅ በእድገት መራመድ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሀዘናቸውን ደስታቸውን ንዴታቸውን ቁጭታቸውን ትዝታቸውን ተሳፋቸውን በአጠቃላይ ማንነታቸውንና ስሜታቸውን የሚያንፀባርቁበት አካላዊ ክዋኔ ነው፡፡

ስለ ትያትርና ፊልም ምንነት ለመረዳት በመጀመሪያ ስለ ትወና፣ ድርሰት፤ እና የትያትርና የፊልም አዘገጃጀት በመረዳት በተገቢ ሁኔታ ታውቃላችሁ፡፡ ስለሆነም በዚህ ክፍል ተማሪዎች እነዚህን ጥበባት ከተማራችሁ በኋላ የተረዳችሁትን ትተነትናላችሁ፤ ታስረዳላችሁ፡፡

የአካባቢ ጥበቃ የንጹህ ውሃ መጠጥ አቅርቦትና የአካባቢ ቆሻሻ ፍሳሽ አወጋገድ ላይ ሲያተኩር ሰፋ ባለ መልኩ የአካባቢ ብክለት የሚያስከትሉት ለጤና ጠንቅ የሆኑ ጎጂ ኬሚካሎችንና ቆሻሻዋችን መቆጣጠርና ማስወገድን ይመለከታል፡፡

የሙዚቃ ትምህርት አምስቱን የሰሜት ህዋሳትን በማነቃቃት የአእምሮ ፈጣን አዛዥነትን የሚያጎለብት በመሆኑ ማሠብን ማመዛዘን የመረዳት ችሎታን ማጎልበት በራስ መተማመን መንፈስን፤ ችሎታን ማዳበር ትኩረት ማድረግና የማስታወስ ችሎታን ይጨምራል፡፡ የውዝዋዜ ትምህርት የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ጋር ቁርኝት አለው ይህም የድርጊት ገላጭ እንደመሆኑ ለምሳሌ ስለፆታ እኩልነት ፤ስለስርአተ ፆታ ፤ስለጥንቃቄ ወዘተ በአጠቃላይ ከትምህርቶች ጋር ጥምረት ያለው ገላጭና አስተማሪ ነው፡፡

በዚህ ክፍል ለትግበራ የቀረበው አጭር ተውኔት ችግኝ መትከል ለሀገር የሚሰጠውን ጠቀሜታና አገር ከምንም በላይ መሆኗን ለማሳየት የተፃፈ ሲሆን ከአሁን በፊት የተማራችኋቸውን ትምህርቶች በማቀናጀት በተግባር በመከወን የምታሳዩበትና ስለሀገራችሁ

አውቃችሁ ንቃተ ህሊናችሁን እንድታዳብሩ ታስቦ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ታሪኩን አስፋፍታችሁ በመፃፍ የድርሰት ክህሎታችሁንም ከፍ ታደርጉበታላችሁ፡፡
እንደሚታወቀው የክወናና ዕይታጥበብ ዘርፍ በስው ልጆች የታወቀ እውቀት ነው፡፡ ከጥገኝነት አንስቶ በየጊዜውና በየዘመናቱ የሰው ልጆችን ስልጣኔ ተከትለው የተለያዩ ጥበባዊ ዘርፎች ተፈጥርዋል ያረጁት ተትተዋል፡፡ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ጋር ባለው ከፍተኛ ቁርጠኝነት በተለያዩ ጊዜያት የየዕለት ተዕለት ሕይወ ታችን እንቅስቃሴ ውስጥ የሚረዱን የመንገድ የትራፊክ ጠቃሚ ምልክቶች ባለሁለት ቀለም ምልክቶች ይጠቀሳሉ ከእነዚህ ምልክቶች ምን ያክል እናውቃቸዋለን የትኛውም ማህበረ ስለ አካባቢው የሚገኙ ምልክቶችን ለይቶ ያቃቸዋል ይህንን የግንዛቤ እጥረት በመቀየር በዓለም አቀፉ መግባቢያ የሆኑ ምልክቶችና አርማዎችን በዚህ የ6ኛ ክፍል የዕይታ ጥበብ ትምህርት መማሪያ የተዘጋጀው መጸሐፍ ሲሆን መስረታዊ የክወናና የዕይታ ጥበብ ትምህርትን አካቶ ይዟል፡፡

## ከዚህ የክፍል ደረጃ በኋላ ተማሪዎች የሚከተለትን ይችላሉ

- ቀላል የሆኑ የክወና እና እይታ ጥበባትን (መስመር፣ ቅርፅ፣ ፍርም፣ ቀለም፣ እሴት፣ በይዘት፣ሻካራነትና ልስላሴ፣በመጠን፣በሀረግ)ትለያላችሁ::
- የቲያትር፣ የቪዱዮ ቀረፃ ዘዴ፣ትለያላችሁ::
- ቀላል የሙዚቃ አላባዊያንን ሪትምን፣ዲይናሚክ/ሃይለ ድምፅን/፣ ቴምፖ / የፍጥነት ሌክት፣ ፒች/ የክረት መጠን/ ወዘተ..ትለያላችሁ::
- ቀላልየውዝዋዜ ላባዊያንን ዘዴ ትለያላችሁ::
- ቀላል የሙዙቃ ኖታዎችን ታነባላችሁ::
- የተዘረዘሩትን እና የተመለከቱትን መልዕክቶች ትተረጉማላችሁ::
- አንድን ድምፅና ምስል ከተመለከቱና ካዳመጡ በኃላ ምስሎችንና ድርጊቶችን ትለያላችሁ::
- ቀጭንና ወፍራም ክረቶችን ትለያላችሁ::
- የቁልፍ ምልክቶችን /ኪሲግኒቸሮችን/ ትለያላችሁ::
- በሜጀርና በማይነር ስኬል መሃከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ትገልፃላችሁ::
- በቲያትር ጥበባት ውስጥ /በድርጊት፣ በመመራት፣ጭዋታን በመፃፍና፣ በፊልም ጥበባት መሃከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ታብራራላችሁ ታሳያላችሁ::
- በስታፍ ላይ በትሬብል ክሌፍና በቤዜ ክሌፍ የተፃፈ ቀላል ዜማዎችና ምቶችን ትከውናላችሁ::
- በቀጭንና በወፍራም ክረቶች መሃከል ያለውን ልዩነት ትለያላችሁ::
- የስዕል፣የቀለም ቅብና የህትመት ክህሎቶቻቸውን ያሳያሉ::
- ድምጽ አልባ ድራማ ማይም ታዳብራላችሁ::
- ተቆራርጠው የተቀመጡትን የሙዚቃ ምልክቶች በመገጣጠም ትሰራላችሁ::
- ስሜቶችን፣ ሃሳባቸውን፣ፍላጎታቸውን እና ጭብጦችን በሙዙቃ፣ በቲያትር፣ በቪዲዮ፣ በፍቶግራፍ፣በውዝዋዜ ትገልፃላችሁ::

# ምዕራፍ 1

# ጥበባዊ ግንዛቤ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ጥበባዊ ግንዛቤን የጥበባት ተፈጥሮ በሚል በሙዚቃ፣ በውዝዋዜ፣ በቴአትርና በእይታ ጥበብ የተለያዩ ትምህርቶች ተካተዋል፡፡ ከእነርሱም ውስጥ የሜጀርና የማይነር ስኬሎች ክረቶችና የቁልፍ ምልክቶች (Key signatures)፣ የቴአትር ጥበባት ድርጊት መምራት፣ ጨዋታ መጻፍና የፊልም ጥበባት እንዲሁም በቀለም ቅብና በሌሎች የእይታ ጥበባት መሠረት ሥዕሎችን መሣል ተካተውበታል፡፡

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- መሰረታዊ የሆኑትን የስኬል ክፍሎችን ታውቃላችሁ፡፡
- የቁልፍ ምልክቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የቁልፍ ምልክቶችን በስታፍ ላይ ትፅፋላችሁ፡፡



### 1.1.1. የዲያቶኒክ ሜጀር ስኬል

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ⊙ የድምፅ ርቀቶችን ትረዳላችሁ::
- ⊙ የድምፅ አደራደር ቅደም ተከተሎችን ታውቃላችሁ::
- ⊙ የድምፅ ርቀቶችን በድምፃችሁ ትዘምራላችሁ::

**ስኬል** የተለያዩ ድምፆች አደራደር ሥነ ጥበባዊ ቅንብር ውጤት ሲሆን በተለያዩ ክፍሎች ይመደባል::

**ሜጀር ስኬል** በ 3 - 4 እንደዚሁም 7 - 8 ድምፆች መካከል የግማሽ ድምፅ እርቀት ሲገኝ በመውጣትና በመውረድ (Ascending and descending order) እንጫወታለን

C - D - E - F - G - A - B - C

1 2 3 4 5 6 7 1or8th

1 1 ½ 1 1 1 ½



**የሻርፕ ቁልፍ** እስኬሎችን ከአንዱ ሜጀር ወደ ሚቀጥለው ስኬል ለመገንባት ፐርፌክት ፊፍዝ (P5th) ወደፊት በመቁጠር እናገኛለን

የሻርፕ መለያ ቁልፎች F♯ , C♯ , G♯ , D♯ , A♯ , E♯ , B♯

| ቁጥር | ሜጀር | ማይነር | መለያ ቁልፎች |
|---|---|---|---|
| 0 | C | a | -------- |
| 1 | G | e | F♯ |
| 2 | D | b | F♯ , C♯ |
| 3 | A | f♯ | F♯ , C♯ , G♯ |
| 4 | E | c♯ | F♯ , C♯ , G♯ , D♯ |
| 5 | B | g♯ | F♯ , C♯ , G♯ , D♯ , A♯ |
| 6 | F♯ | d♯ | F♯ , C♯ , G♯ , D♯ , A♯ , E♯ |
| 7 | C♯ | a♯ | F♯ , C♯ , G♯ , D♯ , A♯ , E♯ , B♯ |

የፍላት ቁልፍ እስኬሎችን ከአንዱ ሜጀር ወደ ሚቀጥለው ለመገንባት ፐርፌክት ፎርዝ (P4th) ወደፊት በመቁጠር እናገኛለን

የፍላት መለያ ቁልፎች B♭, E♭, A♭, D♭, G♭, C♭, F♭

## 1.1.2 የዲያቶኒክ ማይነር ስኬል

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የማይነር ድምፅ ርቀቶችን ትረዳላችሁ፡፡
- የማይነር ድምፅ አደራደር ቅደም ተከተሎችን ታውቃላችሁ፡፡
- የማይነር ድምፅ ርቀቶችን በድምፅ ትዘምራላችሁ፡፡

ማይነር እስኬል በሶስት ምድቦች ይከፈላል

- ናቹራል /Natural minor/
- ሐርሞኒክ /Harmonic minor/
- ሜሎዲክ /Melodic minor/

ሀ. ናቹራል (Natural minor) ስኬል በ 2 - 3 እንደዚሁም 5 - 6 የድምፅ ርቀቶች መካከል የግማሽ ድምፅ½ (semitoneor half tone) በተቀሩት (1) የሙሉ ድምፅ (Toneor whole tone) እርቀት ሲገኝ በመውጣትና በመውረድ (Ascending and descending order) እንጫወታለን

a - b - c - d - e - f - g - a

1 2 3 4 5 6 7 1or8th

1 ½ 1 1 ½ 1 1




ለ. ሓርሞኒክ (Harmonic minor) ስኬል በ 2 - 3 ፣ 5 - 6 እንደዚሁም 7 - 8 የድምፅ ርቀቶች መካከል የግማሽ ድምፅ½ (semitoneor half tone) በተቀሩት (1)የሙሉ ድምፅ (Toneor whole tone) እርቀት ሲገኝ በመውጣትና በመውረድ (Ascending and descending order) ስንጫወት
የሰባተኛውን ድምፅ በግማሽ ድምፅ በመጨመር ይሆናል

a - b - c - d - e - f - g#- a

1 2 3 4 5 6 7 1or8th

1 ½ 1 1 ½ 1 ½




ሐ. ሜሎዲክ (Melodic minor) ስኬል በ 2 - 3 እንደዚሁም 7 - 8 የድምፅ ርቀቶች መካከል የግማሽ ድምፅ½ (semitoneor half tone) በተቀሩት (1) የሙሉ ድምፅ (Toneor whole tone) እርቀት በመውጣት (Ascending) ሲገኝ በመውረድ (descending order) በ (Natural minor) እንጫወታለን

a - b - c - d - e - f# - g#- a

መውጣት

1 2 3 4 5 6 7 1or8th

1 ½ 1 1 1 1 ½

a - b - c - d - e - f - g - a

መውረድ

1 2 3 4 5 6 7 1or8th

1 ½ 1 1 ½ 1 1

## 1.1.3 የቁልፍ ምልክቶች (Key signatures)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ⊙ የሻርፕ ሜጀር ስኬሎች ቁልፎችን ትለያላችሁ፡፡
- ⊙ የሻርፕ ማይነር ስኬሎች ቁልፎችን ትለያላችሁ፡፡
- ⊙ የፍላት ሜጀር ስኬሎች ቁልፎችን ትለያላችሁ፡፡
- ⊙ የፍላት ማይነር ስኬሎች ቁልፎችን ትለያላችሁ፡፡

## የቁልፍ ምልክቶች በጂ ስታፍ ላይ



## የቁልፍ ምልክቶች በኤፍ ስታፍ ላይ

1. 

2. 

3. 

4. 

5. 

6. 

7. 

## መልመጃ

**I የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልሳቸውን ምረጥ /ጭ/**

1.ሶስት ፍላት መለያ ቁልፍ ያለው ሜጀር ስኬል

ሀ.E♭ ለ.C♭ ሐA♭ መ.B♭

2.የኤ ሜጀር ስኬል መለያ ቁልፍ

ሀ.  ለ.  ሐ  መ. 

3. የ C ሜጀር ስኬል የፊደል አደራደር

ሀ. ABCDEFGA ለ.CDEFGABC ሐ.CEG መ.CDEFG

4.የሜጀር እስኬል የድምፅ እርቀት ቅደም ተከተል

ሀ. Tone, Tone, Semitone, Tone, Tone, Tone, Semitone
ለ. Tone, Semitone, Tone, Semitone, Tone, Tone, Semitone
ሐ. Tone, Tone, Tone, Semitone, Tone, Tone Semitone
መ. Semitone, Tone, Tone Semitone, Tone, Tone, Tone,

5. የናቹራል ማይነር ስኬል የድምፅ ርቀት ቅደም ተከተል

ሀ. Tone, Tone, Semitone, Tone, Tone, Tone, Semitone
ለ. Tone, Semitone, Tone, Semitone, Tone, Tone, Semitone
ሐ. Tone, Semitone,Tone, Tone, Semitone, Tone, Tone
መ. Semitone, Tone, Tone Semitone, Tone, Tone, Tone

**II. ከዚህ በታች በሰታፍ ላይ የተፃፉትን መለያ ቁልፎች ሜጀራቸውንና ማይነራቸውን ፃፍ**




______ ______ ______ ______ ______ ______ ______ ______

**III. ከዚህ በታች የተፃፉትን ስኬሎች ፊደላት በተሟላ የፊደል አደራደራቸውን በቅደም ተከተል ፃፉ**

1. G
2. f #ሀርሞኒክ
3. B

4. E
5. d





ውዝዋዜ ወይም ዳንስ የስው ልጅ በእድገት መራመድ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሃዘናቸውን ደስታቸውን ንዴታቸውን ቁጭታቸውን ትዝታቸውን ተስፋቸውን በአጠቃላይ ማንነታቸውንና ስሜታቸውን የሚያንፀባርቁበት አካላዊ ክዋኔ ነው።

- ባህላዊ
- ባህል ዘመናዊ
- ዘመናዊ

አላማ

ተማሪዎች ስለውዝዋዜ አይነት እንዲያውቁ ማድረግ

ዝርዝር ዓላማ

- ባህላዊ
- ባህል ዘመናዊ
- ዘመናዊ

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ሦስቱን የባህል ክፍሎች ታውቃላችሁ።
- ዝርዝር ሀሳባቸውን ትለያላችሁ።

**ባህላዊ** ውዝዋዜ የሀገራችን ወግ ባህል ትውፊት በጠበቀ መልኩ የሚደረግ እንደ ብሄር እንደ በሄረሰቡየሚለያይ የውዝዋዜ አይነት ሲሆን በአንገት በትከሻ በወገብ በመቀመጫ በዕግር የሚከወን የውዝዋዜ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል።

**ባህል ዘመናዊ** ባህላዊና ዘመናዊ ክዋኔዎች በማጣመር አዲስ የውዝዋዜ ቅርፅን የሚፈጥር የውዝዋዜ ዓይነት ነው።

**ዘመናዊ** የተለያዩ የአካላዊ እንቅስቃሴ የቦታ አጠቃቀም የሚይዝ እንደየዘመኑና የስልተ ምት አይነቱ የሚለዋወጥ በየጊዜው የሚፈጠርየውዝዋዜ አይነት ነው።

በባህላዊ ውዝዋዜያችን ውስጥ አካለዊ እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ የሚጠሩ የተለያዩ የውዝዋዜ አይነቶች አሉእነሱም

መንጥቅ ትከሻን ወደላይ በማድረግና በመመንጠቅ የሚከወን የውዝዋዜ አይነት ሲሆን ከእግርም ወደ ላይ መዝለልን ይጨምራል።

ደስቅ ትከሻን ወደታች እየደፈቁ በማወዛወዝ የሚፈጠር የስክስታ ዓይነት ነው።

ዋንጫ ለቅልቅ አንገትን ወደላና ወደ ታች በማንቀጥቀጥና በማሽከርከር የሚከወን የውዝዋዜ ዓይነቶች ነው።

እንቀጥቅጥ ትከሻንና መላው ሰውነትን እጅን ወደታች በመወጠር የሚከወን ሰውነትን በሙሉ ማቀናጀትን የሚጠይቅ ሀገር በቀል የውዝዋዜ ዓይነት ነው።

**መልመጃ**

**ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐስት በማለት መልሰ ስጡ**

1.እንቅጥቅጥ ከአንገት በላይ የሚደረግ የውዝዋዜ ዓይነት ነው።

2.የመንጠቅ እስክስታ ትከሻን ወደታች በመድፈቅ ይከወናል።

3.ዘመናዊ ውዝዋዜ ዘመናዊነትን ከባህል ጋር አጣምሮ ይሰራል።

4.በውዝዋዜ ሀዘንን መግለፅ ይቻላል።

5. ባህላዊ ውዝዋዜ እንደየዘመኑ ይቀያየራል።

6.ዋንጫ ለቅልቅ አንገትን መሰረት ያደረገ ነው።

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-



- ስለትያትር ተፈጥሮ ትችላላችሁ፡፡
- ተውኔት ምንነት ትችላላችሁ፡፡
- የተውኔት አላባውያን ትችላላችሁ፡፡
- የትወና ምንነት ትችላላችሁ፡፡
- የአተዋወን ዘዴዎች ትችላላችሁ፡፡
- የትያትርና ፊልም አዘገጃጀት ምንነትን ተረድታችሁ ማስረዳት ትችላላችሁ፡፡

የትያትር አፈጣጠር የሰው ልጆች አብረው መኖር ሲጀምሩ በሚያደርጓቸው የተለያዩ ተግባራት እና የእርስበርስ ግንኙነቶች ክዋኔወችን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ማንነታቸውን ለማሳወቅ፣ እርስበርስ ለመግባባት እን ስራ ለመስራት፣ ለመዝናናት፣ ባህላቸውንና ልማዳቸውን ለማጋራት፣ ስለተፈጥሮ ለማወቅ እንዲሁም ታሪካቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ ትውፊታዊ በሆነ መንገድ በማስተላለፍ ሂደት ትያትር እንደተፈጠረ የዘርፉ ምሁራን በተለያዩ መጽሐፍት ገልጸውታል፡፡
የዘመናዊ ትያትርን ጅማሮን ስንመለከት በጥንታዊት ግሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ዓ.ም አካባቢ ለአማልዕክቶቻቸው በሚያደርጓቸው ልዩልዩ ከበራዎች ጋር ተያይዞ እንደተጀመረ የተለያዩ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ ደግሞ ዘመናዊ ትያትር የተጀመረበትን ጊዜ በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን የተለያየ ዘመን ቢያስቀምጡም ድርሰቱ ተጽፎ የሚገኘውና በሀገራችን ለትያትር ጽሁፍ የመጀመሪያ የሆነው የአውሮፓወች ኮሜዲያን መሳለቂያ በ1913 ዓ.ም በቤጅሮንድ ተክለሃዋርያት ተክለማርያም አማካኝነት እንደሆነ በተለያዩ መጽሄቶች እና መጽሐፎች ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡

ትያትር ለተለያዩ ተግባራት ማለትም ለፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ነገሮች አስተማሪ እና አዝናኝ በሆነ መልኩ ይቀርብበታል፡፡ እነዚህን ተግባራት በትያትር ለማቅረብ ደግሞ መሰረታዊ የሆኑት ድርሰት፣ትወና፣ እና ዝግጅት ያስፈልጉታል፡፡

## 1.3.1 ድርሰት

በደራሲው አማካኝነት የሚጻፍ ከማህበረሰቡ ተወስዶ ለማህበረሰቡ የሚቀርብ ታሪካዊ፣ ትውፊታዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ እንዲሁም ምናባዊ ፈጠራዎች የሚቀርቡበት ሲሆን በተለያዩ የአጻጻፍ ዘዴዎች ለመድረክ፣ ለቴሌቪዥን፣ ለሬዲዮ፣ለፊልም፣ ወይም ለልቦለድ በሚሆን መልኩ ሊጻፍ ይችላል፡፡

የመድረክ ተውኔት አጻጻፍ

የተውኔት ምንነት

ተውኔት የሰው ልጆችን የእለት ተእለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ የሚከወን ታሪክ ነው፡፡

ድራማ ማለት (drain) ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ማድረግ ወይም መከወን ማለት ነው፡፡

## 1.3.2 የተውኔት አላባውያን

### ሀ. መቼት

መቼት = መቼ፡ የት፡ እና ማህበራዊ እውነታ የሚሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን ተፈጥሯዊ ተውኔታዊ እንዲሁም አጠቃላይ እና ውሱን ተብለው ከሚያጠቃልሉት ጊዜ እና ቦታ አንጻር ይከፋፈላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከቦታ አንጻር የቤት ውስጥ፤ ከቤት ውጪ፤ ልዩ ልዩ እና ባዶ መቼት በመባል ይታወቃሉ፡፡

### ለ. ገጸባህርይ

ተውኔቱን ለማራመድ በጸሐፊ ተውኔቱ የተፈጠሩ የድርሰት ዓለም ፍጡራን ናቸው፡፡ ከሚሰጣቸው ሚና እና ባህርይ አንጻርም እንደሚከተለው ይከፋፈላሉ፦

ወጥ _ አስተኔ

ወጥ፡- የተውኔቱ ታሪክ ዋና ገጸባህሪ ሆኖ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ታሪኩን ይዞ የሚዘልቅ ሲሆን

አስተኔ፡-በተውኔቱ ታሪክ ውሰጥ ብዙ ሚና የሌለው እና ለዋናው ገጸባህሪ እንዳጃቢነት የሚያገለግል ነው፡፡

አቀንቃኝ _ ፀረ አቀንቃኝ

አቀንቃኝ፡-ያሰበውን አላማና ግብ ለማሳካት እስከመጨረሻው የሚተጋ ገጸባህሪ ሲሆን

ጻረ-አቀንቃኝ(ተቀናቃኝ)፡-ያቀንቃኙን ገጸባህሪ አላማና ግብ የሚጻረርና ለማደናቀፍ የሚጥር ገጸባህሪ ነው፡፡

ሰናይ _ እኩይ

ሰናይ፡-ከቃሉ መረዳት እንደሚቻለው መልካም ባህሪ የሚንፀባረቅበት ገጸባህሪ ሲሆን
እኩይ፡-ሙሉ በሙሉ የሰናይ ገጸባህሪው ተቃራኒ ነው፡፡

ድብቅ _ ግልፅ

ድብቅ፡-ሃሳቡና ፍላጎቱ በግልጽ የማይታወቅ ሲሆን
ግልጽ፡-የድብቅ ገጸባህሪ ተቃረኒ ሆኖ መድረክ ላይ በሚታይበት ጊዜ በቀላሉ የሚታወቅ

ታሪካዊ _ ምናባዊ

ታሪካዊ፡-ከውነተኛ ታሪክ ውስጥ የተወሰደ
ምናባዊ፡-በደራሲው አእምሮ(ምናብ) የተፈጠረ

ሀበርት ሀፍነር የተባለው የተውኔት ባለሙያ ባስቀመጠው የአሳሳል ደረጃ ደግሞ በአራት መልኩ ይገለጻሉ፡፡ እነሱም፦ አካላዊ፤ ማህበራዊ፤ ስነ_ልቦናዊ እና ሞራላዊ የአሳሳል ደረጃዎች በመባል ይታዎቃሉ፡፡

ሐ. ቃለተውኔት የተውኔት ቋንቋ ወይም ገፀ_ባህርያት የሚያደርጉት ምልልስ ሲሆን ከተራው ንግግርም በሚከተሉት ዘዴዎች ይለያሉ፦

ግልፅነት
ተገቢነት እና
ተፈጥሯዊነት

መ. ሴራ

ግጭትን እና ታሪክን አጣምሮ የያዘ ሲሆን ምክንያትን እና ውጤትን አድርጎ በተያያዘ መልኩ ተተንትኖ የሚቀርብበት ነው፡፡

የሴራ ዓይነቶች፦

ልል ሴራ

ያን ያህል የከረረ ግጭት የማይታይበት፤ተመልካችን ጭንቀት ውስጥ የማያስገባ የሴራ አይነት ነው፡፡

ጥብቅ ሴራ

ምክንያትና ውጤቶቹ ጠንካራ እና አሳማኝ የሆነ የሴራ አይነት ነው፡፡

ጥምር ሴራ

ከአንድ በላይ ሴራዎችን አጣምሮ የያዘ ወይም ከዋናው ሴራ ባሻገር ለዋናው ሴራ አጋዥ የሆኑ ተጨማሪ ሴራዎች የያዘ ማለት ነው፡፡

ነጠላ ሴራ እና

በ አንድ ነጠላ ታሪክ ላይ ያተኮረ ተጨማሪ ሴራዎች ላሉት የሴራ አይነት ነው፡፡
ሴራ አልባ ይባላሉ፡፡

ሠ. ጭብጥ

ተውኔቱ ጠቅለል ሲደረግ ሊያስተላልፍ የፈለገው አብይ ጉዳይ፡ ገዥ_ሃሳብ ወይም ዋና ቁምነገር ማለት ነው፡፡

መልመጃ 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነትን እውነት ትክክል ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. መቼት የታሪኩን ቦታ፣ ዘመንና ማህበረሰብ ይገልፃል፡፡
2. ሴራ ምክንያትና ውጤትን የምናይበት ዝርዝር ታሪክ ነው፡፡
3. ጥምር ሴራ አንድ የታሪክ መስመርን ተከትሎ ይጨርሳል፡፡
4. ቃለ ተውኔት ግልፅ መሆን የለበትም፡፡
5. ጭብጥ የተውኔታችንን አብይ ቁምነገር የምናገኝበት የተውኔት አላባ ነው፡፡

### 1.3.3. የተውኔት ዘውጎች (ቴክኒካዊ)

ዘውግ ማለት ፀሀፊ ተውኔቱ አንድን ርዕሰ ጉዳይ መሰረት በማድረግ ፅፎ የሚያቀርበው የተውኔት ዝርያ ማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተውኔት ዘውጎችን በሚከተለው መልኩ ተከፋፍለው እናገኛቸዋለን፦

ሀ. መሪር (tragedy)

አሳዛኝና መሰረታዊ በሆኑ ግጭቶች ላይ በሰው ልጅ ሁለት ፅንፍ ስሜቶች ማለትም በደስታና ሀዘን ዙሪያ የሚያጠነጥን እና መጨረሻው ህሊናን የሚነካ የአጻጻፍ አይነት ነው፡፡ ከሚጠቅማቸው ገፀ_ባህርያት እና ርዕሰ ጉዳዮች አንጻርም ጥንታዊ፡ የመካከለኛው ዘመን እና ዘመናዊ በማለት ይከፋፈላሉ፡፡

ለ. ፍግ (comedy)

እያዝናና እና ሳቅ እያጫረ እንዲሁም የማህበረሰቡን የዕለት ተለት ክዋኔዎችን መርጦና ለይቶ በመንቀስ ቁም ነገርን እያሰጨበጠ ባስደሳች ሁኔታ የሚጠናቀቅ የተውኔት አይነት ነው፡፡

ሐ. ድንቃይ (melodrama)

ከቃሉ መረዳት እንደሚቻለው አስደናቂ ክንውኖች የሚተዩበት የተውኔት አይነት የነበረ ሲሆን ከ 19ኛው መ/ክ.ዘ ወዲህ ከመሪር ተውኔት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በስተመጨረሻ ላይ እኩይ እና ሰናይ ገጸባህሪያት በደግ ስራቸውና ክፉ ምግባራቸው የሚዳኙበት የተውኔት አይነት ነው፡፡የተውኔቱ ታሪክ ባብዛኛው ጊዜ ባጋጣሚዎች ላይ ይመሰረታል፡፡

መ. ቧልታይ (farce)

የማይታመኑና የማይመስሉ ድርጊቶች የሚስተዋሉበት፣ለምን እንዲ ሆነ የሚል ጥያቄ የማይጠይቅ፣በማንኛውም መልኩ ተመልካችን ማሳቅ ብቻ አላማው ያደረገ የተውኔት አይነት ነው

ሠ. ወለፈንዲ (absurd)

ይህ የተውኔት አይነት ከገጸባህሪ አሳሳልም ሆነ ከታሪክ አወቃቀሩ ተስፋቢስነትን፣ተስፋ አስቆራጭነትን፣ውል የለሽነትን የሚያሳይ የተውኔት አይነት ነው።

መልመጃ 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሃሰት በማለት መልሱ።

1. ለማሳቅ ተብሎ የሚፃፍ የተውኔት ዘውግ መሪር ይባላል።
2. ፍግ (ኮሜዲ) እያሳቀ ቁምነገር የሚያስተላልፍ ዘውግ ነው።
3. አሳዛኝ ጅማሮና አስደሳች ፍፃሜ ያለው ቧልት ይባላል።
4. ከንቱነትን የሚያሳየው ዘውግ ወለፈንዲ ይባላል።

ትወና

ትወና ማለት በድርሰት ውስጥ የተወከሉ ገጸ-ባህርያትን በደንብ በማወቅ እና በመረዳት እነሱን ተክቶ ስሜታቸውን መግለጽ፤ድርጊታቸውን መከወን፤ እንዲሁም ሃሳባቸውን በመናገር በተለያዩ መንገዶች የማቅረብ ጥበብ ነው። ይህን ለማድረግ የተለያዩ ጥበባዊ ዘዴዎችን በማወቅ መለማመድ ተገቢ ነው።የማነቃቂያ ልምምዶችንና አእምሮአዊ ዝግጅቶችን ማድረግ

ማስተዋል (consentration)

ዘና ማለት

የፊት ገጽታ ልምምድ ማድረግ

የአካል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ

ቁሳቁስን እንደያዙ በማሰብ በቁሳቁስ የሚሰሩ ነገሮችን መስራት

የመድረክ እንቅስቃሴ ቴክኒኮችን መለየት

Blocking ማለት ሲሆን የትኛውን ቃለ ተውኔት የት ቦታ እንደሚናገሩ፣የትኛውን ግብረ መልስ (Reaction) የቱጋ እንደሚከውኑ የሚለዩበት ነው።

ሚዛናዊነትን የጠበቀ የመድረክ እንቅስቃሴ (stage balance) ቴክኒኮችን መለማመድ የተመልካችን አይን መርጦ የማየት መብት እንዳይጣስ፣ማለትም ተዋንያኑ የፈለጉበት ቦታ እንደፈለጉ ከመንቀሳቀስ ይልቅ ገጸባህሪው ትኩረት ሊያገኝ የሚገባበትን ቦታ ማወቅ እና ,ከቡድን ጋር ተግባብቶ መተወንያስፈልጋል።

## 1.3.4. የተውኔት አዘገጃጀት

የተውኔተ ዝግጅት በሶስት ገጽታዎች የተከፋፈለ ነው፡ ይህም

- ቅድመ ዝግጅት (preproduction)
- ዝግጅት (production)
- ድህረ ዝግጅት (post production) ይባላሉ፡፡

አዘጋጁም እነኚህን ሶስት ገጽታዎች መሰረት አድርጎ የዝግጅት ስራውን ይሰራል፡፡
የተውኔት አዘጋጅ ሚና በቅድመ ዝግጅት ጊዜ (preproduction)

ተውኔቱን በሚገባ መምረጥ
ተውኔቱን በጥልቀት ማንበብና መረዳት
የደራሲውን ዳራ መገንዘብ
ተውኔቱ ወጥና ትርጉም መሆኑን መለየት
ተውኔቱን መተንተን እና ማስታወሻ መያዝ
ተዋንያንን መምረጥ
የፕሮዳክሽኑን ቡድን መምረጥና ማዋቀር

የተውኔት አዘጋጅ ሚና በዝግጅት ጊዜ (during production)

የንባብ ልምምድ መምራትና መቆጣጠር
ድምጻቸውን ማጤን ከገጸባህሪያቱ ጋር መጣጣሙን፣በግልጽና በጉላት መሰማቱን መከታተል
የትንፋሽ ፋታ የሚወስዱበትን፣የድምጽ ውጣ ውረድ የሚኖርበትን ቦታ መቆጣጠር ወዘተ....
የተዋንያንን የመድረክ እንቅስቃሴ (blocking) ልምምዶችን ማስኬድ
ቴክኒካዊ ልምምድ መምራት ይህም ከመምራት ጋር፣ከድምጽ ግብዓት ጋር እና ከማጀቢያ ሙዚቃ ጋር የሚደረገው ልምምድ ነው፡፡
ከአልባሳት ጋር የሚደረግ ልምምድን መምራት

የተውኔት አዘጋጅ ሚና በድህረ ዝግጅት ጊዜ (post production)

ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ከተጠናቀቁ በኃላ ተውኔቱ ለተመልካች የሚቀርብበት ጊዜ ሲሆን በዚህም የታቀዱት ነገሮች ባግባቡ መከወናቸውን ይከታተላል ፣የተሰጡ አስተያየቶችን እየተቀበለ እርምት በመውሰድ ለቀጣይ ስራ ይዘጋጃል፡፡
ፊልም በጽህፈተ ፊልም ውስጥ የተገለጹትን ታሪኮች በመግለጽ ምስል ቀረጻና በተንቀሳቃሽ ምስል ቅንብር አማካኝነት በፈጠራ ክህሎት የማቅረብ እና የመተረጎም ጥበብ ነው፡፡

የፊልም ዝግጅት በ አዘጋጁ መሪነት የሚከወን ጥበብ ነው፡፡ በጽሁፉ ውስጥም የሚከተሉት ግብዓቶችን ይፈጥራል፡፡ እነሱም፡-

ለጸሐፊው ጽህፈተ ፊለም ህይወት ይፈጥራል
ታማኝነት ያለው የዕይታ ሁነት ይፈጥራል
የፊልሙ ታሪክ ወደ ተንቀሳቃሽ ምስል ትርጓሜ ይቀየራል
ለተመልካቹ ስሜታዊ የህይወት ቁርኝት ይፈጥራል
የዝግጅት ባለሙያዎች በጋራ ይሰሩበታል
የፊልም ዝግጅት የእይታ ማዕቀፍ ፈጠራ ተግባር ነው፡፡
ፊለም በውስጡ የሚካተቱ ዋና ዋና የዝግጅት ደረጃወች አሉት፡-
ቅድመ ዝግጅት የሃሳብ ማፍለቂያ ደረጃ
ቅድመ የፊልም ዝግጅት ደረጃ
የፊልም ምርት ዝግጅት ደረጃ
የፊልም ደህረ ዝግጅት ደረጀ

የፊልም ዝግጅት ጽሁፍ ፊልሙን የሚተነትን፤ የሚተረጉም፤ እና ወደ ተንቀሳቃሽ ምስል እይታ የሚቀይር የፊልም አቅርቦት ዋና ዝግጅታዊ ተግባር ነው፡፡

## የመልመጃ 3

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ዘመናዊ ትያትር የተጀመረው በኢጣሊያ ነው፡፡
2. የመጀመሪያው የተውኔት ጸሀፊ በኢትዮጵያ ሀዲስ አለማየሁ ይባላል፡፡
3. የትያትር ጥበብ የተጀመረው ከእምነታዊ ክዋኔወች ነው፡፡

II. የሚከተሉትን ጥያቄወች ትክክለኛ መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የተውኔት ዘውግ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ድንቃይ ለ. ገጸ-ባህርይ ሐ. ሴራ መ. መልስ የለም
2. እያዝናና የሚያስተምር የተውኔት ዘውግ ----- ይባላል?
   ሀ. መሪር ለ. ፍግ ሐ. ቧልታይ መ. ጭብጥ
3.ቃለተውኔት ----- መሆን ይገባዋል?
   ሀ. ተፈጥሯዊ ለ. ተገቢ ሐ. ግልጽ መ. ሁሉም

1. ትውፊታዊ ትያትር የተጀመረው የት ነው?
2. የትያትር ጠቀሜታ ምንድን ነው?
3. የተውኔት ድርሰት አላባውያን ምን ምን ናቸው?
4. በፊልም እና በትያትር መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት አብራሩ፡፡

### ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት



**ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦**

- በቀለም ቅብ የተለያዩ የዕይታ ጥበባት ትስላላችሁ።
- የቀለማትን ባህሪ ትለያላችሁ።
- ሕብረ ቀለምትን አቀላቅላችሁ አዳዲስ ቀለማት ትፈጥራላችሁ
- አንደ ደረጃ ቀለማትን ትለያላችሁ።
- ከአንደኛ ደረጀ ቀለማት ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን አቀላቅላችሁ ትቀባላችሁ።
- አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት በሚቀላቀልበት ጊዜ ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት እንዴት እንደሚ መሰረቱ ታውቃላችሁ።

የሰው ልጅ ሲፈጠር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ በተፈጥሮ ውስጥ እንደሚያገኝ ስለሚያውቅ ከጥንተ ተፈጥሮ ጀምሮ ተፈጥሮን መርምሮ ልብስ፣መጠለያ፣ምግብ ከማድረጉ በተጨማሪ መዝናኛው የአይንና የአእምሮ ምግቡን በዕይታ ጥበባት ዘርፉም ሥዕል፣ቅርፃቅርፅ፣ሕትመት ጥበብ፣ኪነ ሕንፃ የመሳሰሉትን ፈጠራዎችን ከተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መልኩ ቴክኖሎጂዎች እስከ መፍጠር ደርሷል።



ሥዕል፦ከተፈጥሮ የተሰሩ የክውና ና እይታ ጥበባት ንድፍና ዲዛይን

## 1.4.1.ንድፍ /ዲዛይን/

ማለት በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን በቀጥታ በመመልከት ወይም ቀደም ሲል ያስተዋልናቸውንና አእምሮ የመዘገበውን በማስታወስ አልያም ከእውነታው ዓለም ነፁብራቅ ሳንለቅ የግል ፈጠራን በመጠቀም ሀሳባችንን በእርሳስ ወይም በሥዕል ቻርኮል አማካኝነት በወረቀት የምናንፀባርቅበት ለሥዕል ስራ መሰረታዊ ሀሳብ መግለጫ ዘዴ ነው፡፡

1 -የቡድን ፅብረቃ

የመወያያ ጥያቄ

ንድፍ/ዲዛይን/ ማለት ምን ማለት ነዉ ? ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለመምህራቹ ንገሩ፡፡

የሚያስፈልጉ ቋሳቁሶች

እርሳስ፣የስዕል ቻርኮል ከለረ፣ፓስቴል ወረቀት፣የሥዕል ሸራ ወረቀት መለጠፊያ ስሌዳ፣ፕላስተር፣ከተር





የአሰራር ቅዳም ተከተል

1. እርሳሳችን በደንብ ቀርፅን ማዘጋጀት
2. ወረቀታችን በጠንካራ ስሌዳ ላይ ለጥፈን ማዘጋጃት
3. የምንስራውን ሀሳብ በግልፅ መወስን

መልመጃ 1

ሀ. በእውቀት ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች

1 -በአከባቢያችሁ በመዘዋወር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ትኩረት በማስተዋል የሳቡትንና አድናቆት ያሳደረባችሁን ነገሮች በመዘርዘር ለዕይታ ሥራ የምንጠቀምባቸው መሥሪያ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑና በመዘርዘር ተናገሩ ?

መምህር/ት ተማሪዎች አምስተኛ ክፍል ላይ የመሰረታዊ መስመሮች ተምረዋል አሁን ደግሞ በመስመር ንድፍ ብቻ የሰውና እንሰሳትን እንዲሁም ቁሶችን በንድፍ በዚህ መልኩ ትለማመዳላችሁ፡፡

መምህር/ት ተማሪዎች የእጅ መለማመጃ መስመሮች እንዲሰሩ ድጋፍ ያርጉላቸው

የእጅ መለማመጃ መስመሮች







ሥዕል፦የእጅ መለማመጃ መስመሮች







ሥዕል፦ በመስመር የተነደፈ ሥዕል

### የመልክዓ - ምድር አነዳደፍ

የመሬትን ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ የተለያዩ ገጽታ አለው:: ይህን አስተውሎ የተገነዘቡትን በንድፍ ማስቀመጥ ወይም ሥዕል መሥራት የመልክዓ- ምድር ንድፍ ጥናት በመባል ይታወቃል::



ሥዕል፦የመልክዓ ምድር ንድፍ

**ቀለም ቅብ**፡-ሀሳባችንን በንድፍ አማካኝነት በስሌዳ ላይ ካሰፈርን በኋላ ሥዕል ገላጭና የእውነተኛነት ገፅታን ተላብሶ ለተመልካች በሚያረካ መልክ ለማቅረብ የቀለም ቅብ ሥራ ነው:: በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ስትመለከቱ በቴክስቸር ረገድ በተለያዩ ደረጃ የመለስለስና የመሻከር ገፅታ ሲታይባቸው ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊ፣ ነጭና ጥቁር ወዘተ ቀለማትም በላያቸው ላይ ያንፀባርቃል::

የቀለማት ዓይነትና ፀባይ፡-ቀለማት በዓይነታቸው በርካታ ናቸው:: በውል ሰያሜና ደረጃ

ከምንሰጣቸው ጀምሮ ጭራሽ መጠሪያ እስከምናጣላቸው ያሉትን ሁሉ ያጠቃልላል።
ሕብረ ቀለም ማደባለቅ፡-ቀለማት ሲቀላቀሉ አዳዲስ ቀለማት ይፈጥራሉ። በዚህም ምክንያት የተለያዩ ቀለማትን መመሥረት ይቻላል ቀለማት አንዳኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ ደረጃ በመባል በደረጃ ይቀመጣሉ። ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት የሚመሰረቱት ከአንደኛ ደረጃ ወይም መስራች ቀለማት ነው።



ሥዕል፡- ሕብረቀለማት

የቀለማት ዓይነትና ፀባይ፡-ቀለማት በአይነታቸው በርካታ ናቸው። በውል ሰያሜና ደረጃ ከምንሰጣቸው ጀምሮ ጭራሽ መጠሪያ እስከምናጣላቸው ያሉትን ሁሉ ያጠቃልላል። እነዚህ በርካታ ቀለማት በአካባቢያችን በሚገኙ የተፈጥሮና ሰዉ ስራሽ አካላት ላይ ተንፀባርቀው ይታያሉ።
ሕብረ ቀለም ማደባለቅ፡-ቀለማት ሲቀላቀሉ አዳዲስ ቀለማት ይፈጥራሉ። በዚህም ምክንያት የተለያዩ ቀለማትን መመሥረት ይቻላል።
ቀለማት አንዳኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ ደረጃ በመባል በደረጃይ ቀመጣሉ። ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት የሚመሰረቱት ከአንደኛ ደረጃ ወይም መስራች ቀለማት ነው።




ሥዕል፡- የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት




ሥዕል፡-ሞቃት ቀለማት ቀዝቃዛ ቀለማት





## ምልምጃ 2

**የሚከተሉትን ሥዕላዊ ጥያቄዎች በማስተዋል መልሱ**



### የምዕራፉ ማጠቃለያ

የሰው ልጅ ሲፈጠር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ በተፈጥሮ ውስጥ እንደሚያገኝ ስለሚያውቅ ከጥንተ ተፈጥሮ ጀምሮ ተፈጥሮን መርምሮ ልብስ፣ መጠለያ፣ ምግብ ከማድረጉ በተፈጨማሪ መዝናኛው የአይንና የአእምሮ ምግቡን በክወናና ዕይታ ጥበባት ዘርፉም ሥዕል፣ ቅርፃቅርፅ፣ ሕትመት ጥበብ፣ ኪነሕንፃ የመሳሰሉትን ፈጠራዎችን ከተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መልኩ ቴክኖሎጂዎች እስከመፍጠር ደርሰዋል፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ - በእውቀትላይየተመሰረቱጥያቄዎች

1 -ሞቃት ቀለማትን ዘርዝራችሁ አብራሩ ?

2 -ቀዝቃዛ ቀለማት የሚባሉትን ላዮ ?

3 -ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን እንዴት ከየት ተገኙ?

ለ -የግል ፅብረቃ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማትን በወረቀት ላይ ቀብታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ?
2. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ከአንደኛ ደረጃ ሕብረ በወረቀት ላይ ቀብታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ
3. ሦስተኛ ደረጃ ሕብረ ቀለማት ስንት ናቸው በተግባር በወረቀት ላይ ቀብታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ?

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

__________1. መቼት የታሪኩን ቦታ፣ ዘመንና ማህበረሰብ ይገልፃል፡፡

__________2. ሴራ ምክንያትና ውጤትን የምናይበት ዝርዝር ታሪክ ነው፡፡

__________3. ጥምር ሴራ አንድ የታሪክ መስመርን ተከትሎ ይጨርሳል፡፡



# ምዕራፍ

ምዕራፍ ሁለት ፈጠራን መግለጽ

2

# ፈጠራን መግለጽ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የሚያተኩረው ሙዚቃ ኖቶችን የሙሉ የግማሽ የሩብ የአንድ ስምንተኛ የአንድ አስራስድስተኛ በስብስብ መልክ በጊዜ መለያ አማካኝነት እንዲያነቡ ማድረግ በተጨማሪም በሰሌዳላይ የተፃፉ ዜማዎችን እንዲጫወቱ ማድረግ፡፡
አንድን ሙዚቃ ወይም ዜማ በተቀመጠለት የጊዜ ቆይታ መሰረት ስንጫወት በእንቅስቃሴ ቢሆን በቀላሉ ልንረዳው እንችላላን፡፡
ትያትር (ፊልም) ለመስራት እና ለመጻፍ (ደራሲዎች) የትወናን ምንነት፤ ገጸ- ባህርያትን ሃሳብ ማግኛ መንገዶችንና ሃሳብ እንዴት እንደሚፈጠር ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ተረድቶ በመጻፍ ለመከወን ወይም፣ ፓንቶ ማይም እና ድንገቴ ፈጠራን በመጠቀም ጽፎ የገጸ-ባህርያትን ማንነት ለመላበስ ደግሞ መሰረታዊ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡
ከ5 ተኛ ክፍል በተያያዘና ቀጣይነት ባለው መልኩ የንድፍ ጥበብ ፅንስ ሀሳብና የተግባር ትምህርት በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ለ6ኛ ክፍል በሚመጥን መልኩ ተዘጋጀቷል፡፡ በመሆኑም የንድፍ ትምህርት ግንዛቤ ተከታታይ የሆነ የንድፍ ልምምድን የሚጠይቅ እና ይህም የንድፍ ክህሎት የሁሉም የሥነ-ጥበብ ሙያ ዘርፎች መሰረታዊ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች አስፈላጊውን የመማሪያ ቁሳቁስ ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

ጠራን መግለጽ

## 2.1 ስልተምት ከሆሄያት ጋር መቁጠር

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- 4/4 3/4 2/4 6/8 የተፃፉ ኖቶችን ባላቸው የጊዜ ቆይታ መሰረት ታነባላችሁ፡፡
- በስታፍ ላይ ትሬብልና በቤዝ ቁልፍ የተፃፉ ኖቶችን ታነባላችሁ፡፡

ሀ. የሙሉ ድምፅ ኖታዎችንና የሙሉ ዕረፍት ኖታዎችን መቁጠር




ለ. የሙሉ፣ የግማሽ፣ የሩብና የአንድ ስምንተኛ የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታን መቁጠር












### 2.1.1 የተጻፉትን ምቶች በመቁጠር ተለማመዱ












**መልመጃ**

ከዚህ በታች የተፃፉትን የኖት ምልክቶች በባር መስመር ለዩ



ሐ. ከዚህ በታች ለተፃፉት ኖታ ምልክቶች ጊዜ መለያ ምልክቶችን ፃፉ

1. 

2. 

3. 

4. 

## 2.1.2. በትሬብል ክሌፍና በቤዝ ክሌፍ ስታፍ ላይ የተፃፉ ኖቶችን ማንበብ







### 2.1.3. የቀጭንና የወፍራም ድምፅ ክረቶች

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

➲ በድምጾች መካካል ያለውን ርቀት በሚገባ ትለያላችሁ።

በቀጭንና ወፍራም ድምፆች መካከል ያለው የርቀት ደረጃ በሚገባ ለመለየት የሚያስችለን የድምፆች እርቀት (ኢንተር ቫል) በሚገባ ስንመለከት በሁለት ድምፆች መካከል ፊደሎች ቁጥር ብዛት ያለ የድምፅ ወሰነ ርቀት ማለት ሲሆን ከአንድ ድምፅ ተነስተን እስከ ቀጣዩ ድምፅ ድረስ ያለውን ዝምድና የምናውቅበት ዘዴ ነው። ኢንተርቫል በሁለት ምድብ የሚለይ ሲሆን እነሱም ሲምፐል እና ኮምፓውንድ ይባላሉ ። ሲምፐል ኢንተርቫል ስንል እስከ አንድ ኦክታቭ ያለውን ሲሆን ከኦክታቭ በላይ ያለውን ደግሞ ኮምፓውንድ ኢንተርቫል እንለዋለን።

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| C - | D - | E - | F - | G - | A - | B - | C |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 1or8th |
| 1 | 1 | ½ | 1 | 1 | 1 | ½ | |










## 2.2. በውዝዋዜ ስልተ ምትን መረዳት

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የስልተ ምት እንቅስቃሴ በሙሉ የስልተ ምት ውጤት መሆኑን ትረዳላችሁ

**አላማው**

ከላይ የተፃፈውን የልደት መዝሙር በምትዘምሩበት ጊዜ እጃችሁን በማወዛወዝና አካላችሁን በማንቀሳቀስ ዘምሩ፡፡ በዚህን ጊዜ የደከመ አዕምሮ ማንቃት የዛለ ሰውነትን ማፍታታት ትችላላችሁ፡፡



መምህራችሁ የሚያስተምሩትን የኖታ ንባብ ስትቆጥሩ በዋጋቸው መሰረት ከእንቅስቃሴ ጋር አብራችሁ ቁጠሩ::

### 2.3.1. ንግግር አልባ ትወናዎች

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

**ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- ስለንግግር አልባ ትወናዎች ታውቃላችሁ::
- ማይም ድራማን ትተውናላችሁ::
- ፓንቶ ማይም እና የድንገቴ ፈጠራን ምንነትና ጠቀሜታ ተረድታችሁ የቀረበውን ጅምር ታሪክ በተለያዩ ሀሳቦች ትጨርሳላችሁ::

እነዚህ የትወና አይነቶች ማይም እና ፓንቶ ማይም በመባል የሚታወቁ ሲሆን በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ቅርጽን ሲከተሉ ቆይተዋል::

ጥንታዊ ማይም የተለያዩ ከዋኞችን አጉልተው ሊያሣዩ የሚችሉ ግብዓቶችን ማለትም በቀላሉ ሊለይ በሚችል መልኩ የሚቀቡ የገጽ ቅቦችን ቀለመ ደማቅ አልባሳትን በመጠቀም የተጋነኑ እና ሳቅን ሊያጭሩ የሚችሉ ታሪኮች ያሏቸው ድርጊቶችን ይከውኑበት ነበር:: ይህ የማይም ዓይነት በተለያዩ የማቅረቢያ ቦታወችና ዘዴዎች ማለትም በመንገድ ላይ፣ በመድረክ ላይ እንዲሁም ቴሌ-ቪዥን ከተፈጠረ በኋላ በቴሌ-ቪዥን (ቪደዮ) ሲቀርቡ ቆይተዋል::




የቴቪ. ማይም                    የመንገድ ማይም

ዘመናዊ ማይምን ስንመለከት ግን ምንም አይነት የግብዓት መሳሪያወችን የማይጠቀም ሲሆን ነገሮችን በአእመሮ (በምናብ) በማሰብ ከነገሮች ወይም ሌሎች ተጣማሪ ገጸ-ባህርያት ጋር እጅግ በማጋነን ወይም ደግሞ አሳማኝ በሆነ መልኩ ጅማሮ እድገት እና ፍጻሜ ያለውን ታሪክ አካቶ ይቀርብበታል፡፡ ይህ ማይም እውነተኛና ሊታመኑ የሚቺሉ ታሪኮቸን አለያም በፍጹም የማይታመኑ ድርጊቶችን በጥብቅ እና ልል ሴራዎች በማዋቀር ያቀርባል፡፡

በጥብቅ ሴራ----- ምክንያታዊና ታማኝ ድርጊቶች እና ታሪኮች

በልል ሴራ--------- የማይመስሉ ታሪኮችና ድርጊቶች ይቀርብባቸዋል፡፡

ምሳ. በጥብቅ ሴራ የምንጠቀምባቸውን ሀሳባዊ ነገሮች ልክ እንዳሉ አስመስሎ መስራት ሲሆን

በልል ደግሞ የሚታኘክን ማስቲካ ኳስ አድርጎ መጫወት… ወዘተ. የማይመስሉ ነገሮች ማድረግ ይቻላል፡፡

ፓንቶ ማይም

ይህ የማይም አይነት የተገደቡ ግነቶችን በድርጊቶች ማሳየት ሲፈቅድ ለሆኑ የሚችሉ ግን የተጋነኑ ታሪኮችን ልል ሴራን ተጠቅሞ የሚያቀርብ ሲሆን የተለያዩ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በተገቢው ሁኔታ ይጠቀማል፡፡ ድምጽ ባልተፈጠረበት ዘመን ለጥበቡ አለም ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ ሲሆን ፊልሞች (ቪዲዮዎች) በድርጊት ብቻ ይቀርቡበት ነበር፡፡

ምሳ. የቻርሊ ቻፕሊንን ዘ ማሽን ታይም ተመልከቱ፡፡

አሁንም በዘመናዊ መልክ የድምጽ ግብዓቶች ተጨምረውበት የሚቀርብ ሲሆን በተለይ የመስማት ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ትልቅ የመዝናኛ ጥበብ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡

ምሳ. የሚስተር ቢንን ስራዎች ተመልከቱ፡፡

## 2.3.2 ድንገቴ ፈጠራ

ድንገቴ ፈጠራ የሚባለው ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ሲሆን በተለያዩ መንገዶች ሀሳብ በማፍለቅ በግል ወይም በቡድን በመሆን ታሪክ ፈጥረው የሚከውኑበት ጥበብ ነው፡፡ ይህም ማለት ምንም ዓይነት የድርሰት ጽሁፍ ሳይኖር ከተለያዩ የሀሳብ ማግኛ መንገዶችና ስሜቶች፡ መጣጥፎች፣ ገጸ- ባህርያት፣ ታሪኮች፣ ዜናዎች ወይም ማህበራዊ ክስተቶች በመነሳት ምናባዊ ፈጠራን ተጠቅሞ ድርሰት በማድረግ መከወን ሲሆን ለሌኛው ዓይነት ድንገቴ ፈጠራ ደግሞ ጅምር ታሪኮችን ሞልተን የምንሰራበት ሊሆን ይችላል፡፡

የድንገቴ ፈጠራ በርካታ ጥቅሞች ሲኖሩት መድረክ ላይ እየተወንን ድንገት ቃለ ተውኔቱ ቢጠፋብን አለያም የሆነ ችግር ወይም ክስተት ቢፈጠር

ምሳ. ከተሰጠን ተግባር ውጪ የሆነና፡ አደናቅፎን ብንወድቅ፤ ልብሳችን ቢቀደድ፤ አብሮን የሚሰራው ሰው ቢታመም ወይም ቶሎ ባይገባልን የግል የፈጠራ ችሎታችንን ተጠቅመን ከታሪኩ ጋር ክስተቱን በማዋሀድ ሞልተን ተመልካቹ ሳያውቅብን የሚታየው ክዋኔ እንዲቀጥል በማድረግ እንጠቀምበታለን፡፡

የሚከተለው ቅንጭብ (ጅምር) ታሪክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ከሆነው የጉለሌው ሰካራም ከተሰኘው አጭር ልቦለድ ላይ የተወሰደ ሲሆን ተማሪዎች ታሪኩን አሳድገው እንዲፅፉት እና እንዲከውኑት ይደረግ፡፡

ከዱሮ የእንጨት ጉሙሩክ አጠገብ ወደ ምሥራቅ ሲል ካለው ወንዝ ማዶ ድልድዩን ወደ ምሥራቅ ተሻግሮ መጀመሪያ የሚገኘው አነስተኛ ሳር ክዳን ቤት የተበጀ ቤት ማለት ያ ነው፡፡ በዚያ በቤቱ በዚያ በጉለሌ በሠፈሩ ኖረ፡፡

እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ ቤቱን የሰራው እርሱ ነው፡፡ ዋጋ ከፍሎ አስከድኖታል፡፡ ተበጀን ኩራት ተሰማው፡፡ ቆይቶ ደግሞ አይኖቹ እንባ አዘሉ፡፡ በጉንጨም የእንባ ዘለላ ወረደው፡፡ በግራ እጁ መዳፍ ከጉንጩ የተንከባለለውን እንባ ጨፈለቀው፡፡ ዓይኖቹ እንባ ያፈሰሱ ለራሱ ጎጆ ስላለው ነው፡፡ ሊነገር በማይችል ደስታ ልቡ ተለውሷል፡፡

ዝናም ያባረራቸውም ከቤቱ ጥግ ሊጠለሉ ይችላሉ፡፡ ቤት የእግዚአብሔር ነውና ውሽንፍር እንዳያገኛቸው ከቤት ውስጥ ዝናቡ እስኪያባራ ይቆያሉ፡፡ ተበጀን ‹‹ ቤትህን ይባርክ ›› ሊሉት ነው፡፡እንግዲህ መንገደኛው ሁሉ ‹‹ ይህ የማን ቤት ነው ? ብሎ ሲጠይቅ የተበጀ ሊባል ነው ›› አለ፡፡

ቀጥሎ ደግሞ ‹‹ ተበጀ የትኛው ነው ሲባል ዶሮ ነጋዴው ሊባል ነው ›› አለ፡፡

**የመልመጃ 1**

**I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሃሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. የማይም ትወናን በንግግር መስራት ይቻላል፡፡
2. ፓንቶ ማይም የድምጽ ግብዓትን ይጠቀማል፡፡
3. ፓንቶ ማይምን እጅግ አጋኖ መስራት ይቻላል፡፡

**II. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ(ጭ)**

1. የተለያዩ ስሜቶችን ለመግለጽ የማያገለግለው የቱ ነው?
   ሀ. ትወና ለ. ቪዲዮ ሐ. ፎቶ መ. መልስ የለም
2. እጅግ በማጋነን እና ያለምንም ግነት የምንሰራበት ጥበብ የቱ ነው?
   ሀ. ድንገቴ ፈተራ ለ. ፓንቶ ማይም ሐ. ማይም መ. ሁሉም

## 2.4. ንድፍና ቀለም ቅብ ለህትመት ሥራ

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

**ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የንድፍ ጥበብ ፅንስ ሀሳብና በተግባር ትገነዘባላችሁ፡፡
- ለቀለም ቅብ የሚሆን ንድፍ ጥበባት ትስላላችሁ፡፡
- የቀለማትን ባህሪ ትለያላችሁ፡፡
- ሕብረ ቀለማትን አቀላቅላችሁ አዳዲስ ቀለማት ትፈጥራላችሁ፡፡
- አንደኛ ደረጃ ቀለማትን ትለያላችሁ፡፡
- ከአንደኛ ደረጀ ቀለማት ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን አቀላቅላችሁ ትቀባላችሁ፡፡
- አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት በሚቀላቀለበት ጊዜ ሶስተኛ ደረጃ ቀለማት እዴት እንደሚመሰረቱ ታውቃላችሁ፡፡

ንድፍ ማለት በአካባቢያችን በቀጥታ በመመልከት ወይም ቀደም ሲል ያስተዋልናቸውን እና አእምሮ የመዘገበውን በማስታወስ አልያም ከእውነታው አለም ነፀብራቅ ሳንለቅ የግል ፈጠራን በመጠቀም ሀሳባችንን በእርሳስ ወይም በተለያዩ የንድፍ መሳሪያዎች አማካኝነት በሀሳብ የነበረውን ወደ ዕይታዊ ጥበብ የምንለውጥበት የጥበብ ዘዴ ነው ፡፡
የንድፍ ስራን በተግባር ለማከናወን የምንጠቀምባቸው የተለያዩ መስሪያ ቁሶች አሉ አገልግሎታቸውም የተለያየ ነው ፡፡

ለንድፍ መስሪያነት ከምንጠቀምባቸው መካከል እርሳስ ፣ እስክርቢቶ ፣ ከሰል /ቻርኮል/ ፣ ወረቀት ፣ ቀለማትና ማጣበቂያ ተጠቃሾች ናቸው ።





ሥዕል፦ የተለያዩ ንድፎች

**መልመጃ 1**

**ሀ- የቡድን ጽብረቃ**

የተዘረዘሩትን የሥዕል መሳሪያዎች እንዴት በምን መልክ እንደምትጠቀሙባቸው በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳቹሁበትን ሀሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ

**ለ- የግል ጽብረቃ**

1-የአካባቢን ንፅህና አጠባበቅን የሚያንፀባርቁበት የንድፍ ስራዎችን በየግላችሁ ከስራችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች ገለፃ አድርጉ

## 2.4.1 የርቀትናቅርበት / ዕርዮተአድማስ /

በርቀትና በቅርበት የሚገኙ የተለያዩ መጠን ያላቸዉ ነገሮች በአንድ ላይ ስንመለከት በዕይታችን የሚፈጠር ክስተት መኖሩን ተገንዝባችሁ ታወቃላችሁ:: ራቅ ብሎ የሚገኝ ትልቅ አካል እና በቅርብ የሚገኝ ትንሽ ነገርን በመጠን አያነፃፀራችሁ ተመልከቱና ምን እንደተገነዘባችሁ ተወያዩ ::





ሥዕል፡-የርቀትናቅርበት / ዕርዮተአድማስ /

አንድ ነገር ከእኛ እየራቀ ሲሄድ መጠኑ እያነሰ ቀለሙ እየደበዘዘ መስሎ ይታያል:: በሌላ በኩል ለዕይታችን ቅርብ የሆነ ትንሽ አካል በርቀት ከሚገኝል ትልቅ አካል ጋር ሲነፃፀር ትንሹ ትልቁን የሚበልጥ ወይም እኩል መስሎ ይታያል :: በመሆኑም ንድፍ በምን ስራባት ጊዜ የራቀውን ለማሳነስ የቀረበውን በማጉላት በንድፍችን ውስጥ ርቀትና ቅርበትን ፤ስፍትና ጥልቀትን ለመግለፅ ያስችለናል ::

**መልመጃ 2**

I.ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት መልሱ::

1. የንድፍ ስራን ለመስራት አካባቢያችን ከፍተኛ ሚና አለው::
2. የተፈጥሮንና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ልብ ብለን በማስተዋል በንድፍ መግለጽ ይቻላል::
3. ንድፍ በምንሰራበት ጊዜ የተፈጥሮም የሰውሰራሽም ብርሃን አያስፈልገንም::

4. ለቀለም ቅብና ለህትመት ስራ የምንጠቀመው የንድፍ ዘዴ ይለያያሉ፡፡

II. ለሚከሉት ጥያቄዎችን ትክክለኛ መልስ የያዘውን ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ ለንድፍ መስሪያ የሚያገለግሉትን ግብአቶች የቱ ነው?
   ሀ-እርሳስ ለ-እስክርቢቶ ሐ- ወረቀትና ላጺስ መ- ሁሉም

2. ከሚክተሉት ውስጥ ንድፍን የሚጠቀሙ የተለያዩ ሙያ ዘርፎችመካከል የትኛው ነው?
   ሀ- ለዲዛይን ለ- ዕይታጥበብ ሐ- ለፁሁፍ መ- ሀ እና ለ መልስ ናቸው

3. በዕይታጥበብ ውስጥ ለንድፍ የምንስራቸው ዘዴዎች የሚጠቁመው የቱ ነው?
   ሀ- ለቀለም ቅብ ለ- ለህትመት ሐ- ለእርሳስና እስክርቢቶ መ- ሁሉም

## 2.4.2 ብርሃንና ጥላ

ብርሃን በነገሮች ላይ ሲያርፍ ከብርሃኑ አቅጣጫ በተቃራኒው ጥላ ይወድቃል፡፡ የሚፈጠሩትም ጥላዎች እንደ ብርሃኑ ምንጭ አይነትና በተለያዩ ክስተቶች ምክንያት ልዩነት ሊታይባቸው ይችላል ፡፡ የተፈጥሮ ብርሃን ማለትም የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን በነገሮች ላይ ሲያርፍ የሁሉም ነገር ጥላ ወደ አንድ አቅጣጫ ይወድቃል ለዚህም መረጃ የሚሆነው ጠዋት ላይ ጥላ ወደ ምዕራብ ሲወድቅ ከሰአት በኋላ ደግሞ ወደ ምስራቅ ይወድቃል ፡፡







ሥዕል ፦ በተፈጥሮ ብርሃን የነገሮች የጥላ አወዳደቅ



ሥዕል፦ ለሰው ስራሽ ብርሃን የነገሮች ጥላ አወዳደቅ





ሥዕል :-ለቀለም ቅብ የተዘጋጀ  የንድፎች





ሥዕል :- ለህትመት የተዘጋጀ ንድፎች

## ማጠቃለያ

የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ የሕብረተሰቡና በአካባቢው የሚገኙ ሕይወት ያለቸው ነገሮች ጤናን መጠበቅ ነው :: ቆሻሻን ያለአግባብ ያገኙበት ቦታ መጣል ፣ ከመፀዳጃ ቤት ውጭ መጠቀም የመሳሰሉትን አጉል ልማዶች መፈጸም አካባቢን ለብክለት ይዳርጋል:: ከዚህ ሀሳብ ተነስታችሁ በአካባቢያቹ የታዘባችሁትን ትዝብት ወደ ንድፍ ቀይራችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

በ $\frac{4}{4}$ ፣ $\frac{2}{4}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{6}{8}$ የጊዜ መለያ ምልክቶች የሙሉ፤ የግማሽ፤ ሩብ፤ የአንድ ስምንተኛና የአንድአስራስድስተኛ ባላቸው  የምት ጊዜ  በስታፍ ላይ የተፃፉትን ኖቶች ባላቸው የድምፅ ርቀት መሰረት ማንበብ የተለያዩ ስልተምትን ለመገንዘብ ያስችላል:: ንግግር አልባ የትወና አይነቶች ማይም እና ፓንቶ ማይም በመባል የሚታወቁ ሲሆን በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ቅርጽን ሲከተሉ ቆይተዋል:: ጥንታዊ ማይም የተለያዩ ከዋኞችን አጉልተው ሊያሣዩ የሚችሉ ግብዓቶችን ማለትም በቀላሉ ሊለይ በሚችል መልኩ የሚቀቡ የገጽ ቅቦችን ቀለመ ደማቅ አልባሳትን በመጠቀም የተጋነኑ እና  ሳቅን

ሊያጭሩ የሚችሉ ታሪኮች ያሏቸው ድርጊቶችን የከውኑበት ነበር፡፡ ዘመናዊ ማይምን ስንመለከት ግን ምንም አይነት የግብዓት መሳሪያወችን የማይጠቀም ሲሆን እውነተኛና ሊታመኑ የሚቸሉ ታሪኮቸን አለያም በፍጹም የማይታመኑ ድርጊቶችን በጥብቅ እና ልቅ ሴራዎች በማዋቀር ያቀርባል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ንድፋን የተለያየ የሙያ ዘርፎች ለስራቸው ይጠቀሙበታል ከነዚህም ዉስጥ በዋናነት ሁሉም የክውናና ዕይታ ጥበባት ማለትም ስዕልና ቅርፃቅርፅ፣ ህትመት ጥበብን፣ ግራፊክስ ዲዛይን እንዲሁም የምህንድስና ና ኢንጂነሪን ዘርፎች ይጠቀሙ በታል፡፡ ሀሳባችንን በንድፍ ለማንፀባረቅም የተፈጥሮና ሰው ስራሽ ነገሮች ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው፡፡ ራቅ ብሎ የሚገኙ ትልቅ አካል እና በቅርብ የሚገኝ ትንሽ ነገርን በመጠን እያነፃፀራችሁ ተመልከቱና ምን እንደተገነዘባችሁን አስረዱ፡፡

## ማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት መልሱ፡፡

1. ንድፍን የተለያየ የሙያ ዘርፎች ለመስራት ይጠቀሙበታል፡፡
2. ሀሳባችንን በንድፍ ለማንፀባረቅም የተፈጥሮና ሰው ስራሽ ነገሮች ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው፡፡
3. የሰው ስራሽ ብርሃን ሰንጠቀም የነገሮችን ጥላ እንደ ብርሃኑ አቀጣጫና እንደ ነገሮች አቀማመጥ በተለያዩ አቅጣጫ ሊወድቅ ይችላል፡፡

II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በክፍቱ ቦታ ሙሉ፡፡

1. የ ------ ጥበብ ሀሳብ በማፍለቅ ችግርን ለመፍታት ይጠቅማል፡፡
2. ቁሳቁሶችን በመጠቀም የምንሰራበት ንግግር አለባ ትወና -------ይባላል፡፡
3. ንግግር አልባ ትወና በዋናነት ለ---- ሰዎች ተዝናኖት ይውላል፡፡

# ምዕራፍ 3

## ታሪካዊና ባህላዊ አግባብ/አውድ/

### መግቢያ

ታሪክ የባህል እድገት ውጤት ነው፡፡ ማለትም፣ይህ በሰው ሁሉ የተፈጠረውን እና የተለያዩ አመለካከቶችን፣ እንቅስቃሴዎችን እና እምነቶችን ጨምሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈውን ማንኛውንም ነገር ያካትታል፡፡ ባህል የሰው ልጅን ራስን የመግለፅ እና የራስን ዕውቀት ሁሉንም ቅርጾች እና ዘዴዎችን፣ በሰው እና በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ዘንድ የተሰበሰቡትን ችሎታዎችን ጨምሮ በሁሉም እጅግ በጣም የተለያዩ መገለጫዎች ውስጥ የሰዎች እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡ ሃገራችን ካላት ቀደምት ታሪክ በራሷ አኩሪ ባህል ያላት ድንቅና መስብ የሆነ ተፈጥሮና ፊደላት ዜማ ሙዚቃ ዜጎቿ በባህላቸው መሰረት በራሳቸው የፈጠሩዋቸው ውዝዋዜዎች አሏት፡፡

ተማሪዎች ስለ ታሪክ ካወቃችሁ በኋላ የታሪኩን መሰረታዊ ጉዳዮች ተንትኖ የሚያቀርብልን ታሪክ ነጋሪ (ተራኪ) ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ክፍል የተራኪ ምንነትና የአተራረክ (አቀራረብ) አንፃሮች ተተንትነው ይቀርቡላችኋል፡፡

የዕይታጥበብ ትምህርት ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘቶችንና የአሰራር ልምዶችን አጠናክሮ በማቅረብ የበለጠ የችሎት ና የልምድ የባህርይ ለውጥ እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ተማሪዎች የስሙትንና ያዩትን ታሪኮች በክወናና ዕይታጥበባት ታሪኩን ሳያዛቡ ባህላዊ ቱዉፊቶችን በተገቢው መልኩ በቅደም ተከተል አለባበሳቸውን ታሳያላችሁ፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ከአጠናቀቃችሁ በኋላ

- የሃገራችሁን የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎችን ስሞችና ምድቦች ታውቃላችሁ::
- የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚሰጡትን ጠቀሜታ በሚገባ ትረዳላችሁ::

### 3.1.1. የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች

ድምፃቸው የሚፈጠረው በክሮቹ በሚፈጠር የድምጽ ንዝረት አማካኝነት ነው::

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምፃቸው በድምፅ ሳጥን አማካኝነት ጎልቶ መውጣትን ትረዳላችሁ::
- የአካላት ክፍላቸውን በሚገባ ታውቃላችሁ::

#### 3.1.1.1 በገና






በገና

በገና የድምፅ ሳጥኑ አራት መአዘን የእንጨት ገበቴ ሲሆን ፊት ለፊቱ የከብት ቆዳ

የሚለብስ ከበግ ወይም ከፍየል አንጀት በቀጭኑ ተገምዶ የሚሰራ አስር የጅማት ክሮች ያሉት የመንፈሳዊ ዜማዎችን ለማዜም የሚያገለግል የአጨዋወት ስልቱም በድርድር የሆነ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የሙዚቃ መሣሪያ ነው።

### 3.1.1.2 ክራር











ክራር ከክር የሙዚቃ መሣሪያዎች አንዱና የድምፅ ሳጥኑ ከእንጨት ገበቴ ወይም ከጎድጓዳ ሳህን የሚሰራ ባለስድስት ክር የሆነ ሲሆን በሁለት ምድብ የተከፈለ ሲሆን
1ኛ. አኮስቲክ ድምፁ በድምፅ ሳጥኑ ብቻ ክሩ ቀጭን ፕላስቲክ (አሳ) ገመድ
2ኛ. የጊታር ክር የሚገጠምለት ድምፁ በጊታር ፒክአፕ አማካኝነት በስፒከር የሚወጣ በተለምዶ ኤሌክትሪክ ቤዝና ሊድ ክራር የምንላቸው ናቸው ክራር ለአለማዊውም ሆነ ለመንፈሳዊ ሙዚቃ ስንጠቀምበት አጨዋወቱም በድርድርና በግርፍ ነው።

### 3.1.1.3 መሰንቆ






ማሲንቆ በተለይ በኢትዮጵያ ከሚታወቁት ባለ አንድ ክር ክሩ ከፈረስ ጭራ በቀጭን ተገምዶ የሚዘጋጅ ክብና የአልማዝ ቅርፅ ያለው የድምፅ ሳጥኑ ከእንጨት የሚሰራ፣ የፍየል ወይም የበግ ቆዳ የሚለብስ ፣ከአንድ ወጥ ምሶሶና መቃኛው ድቡልቡል በተቦረቦረው ምሶሶው ጫፍ የሚገባና መጫውቻው (መምቻ) ደጋን ቅርፅ ያለው ለመንፈሳዊና ለአለማዊ አገልግሎት የሚውል የሙዚቃ መሣሪያነው::

### 3.1.1.4 ዱል



ዱል ከክራር መጠኑ ተለቅ የሚል የድምፅ ሳጥኑ ከእንጨት የሚሰራ ፊት ለፊቱ የከብት ቆዳ የሚለብስ አምስት የጅማት ክር ያለው የክርመሣሪያነው::

## 3.1.2 የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች

የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምፃቸው የሚፈጠረው በእስትንፋስ አማካኝነት ነው፡፡

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት
ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-
⊙ የትንፋሽ መሳረያዎች ድምፃቸው በስትንፋስ መውጣትን ትረዳላችሁ፡፡
⊙ የአሰራራቸውን በሚገባ ታውቃላችሁ፡፡








### 3.1.2.1 ዋሽንት

ዋሽንት መጠነኛ ርዝመት ያለው ከትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ ነዉ፡፡ ከሸንበቆ የሚሰራ ባለአራት ቀዳዳዎች ያሉት ሲሆን ቀዳዳዎቹም እንደ የሸንበቆው መርዘምና ማጠር የሚወሰን ነው በገጠር እረኞች በከተማው በአብዛኛው በባህላዊ የሙዚቃ ስብስብ (ባንድ) የመነሻ ድምፅ (ቅኝት) በመስጠትና እንደዚሁም ለመንፈሳዊ ሙዚቃ በአጃቢነት ያገለግላል፡፡

### 3.1.2.2. እምቢልታ




አምቢልታ ጥንታዊ ከሆኑት የትንፋሽ መሳሪዎች አንዱ ነው፡፡ እምቢልታ በሶስት ክፍሎች የሚከፈል በጥንት ጊዜ ለክብረ በዓልና ወደ ጦር ሜዳ ለሚሄዱ አርበኞች ማነቃቅያ የሆነ አድማቂ መሣሪያ ነው፡፡

እምቢልታ በሦስት ክፍሎች ይመደባል

1.መሪ አውራ

2.መካከለኛው ድፍን

3. ረጅሙ ይማ በመባል ይታወቃሉ፡፡

### 3.1.2.1. መለከት






መለከት አንድ ድምፅ ብቻ የሚያወጣና ከጫፍ ላይ የዋንጫ ቅርፅ ያለው በቀደምት ጊዜ ከነጋሪት ጋር በመሆን የመንግሥት አዋጅ እንዲሰማ ትዕዛዝን መስጫ መሣሪያ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ነው፡፡

### 3.1.2.3 ድንኬ



ድንኬ ከቀርከሃ እና ከከብት ቀንድ የሚሰራ ሶስት ሜትር ቁመት ያለው አንድ ዜማ ብቻ መጫወት የሚችል ለሀዘንና ለደስታ የሚጠቀሙበት ጥንታዊ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

### 3.1.2.4 ፋንፋ



ፋንፋ አስራ አንድ አጫጭርና ቀጫጭን ሸንበቆዎች ተጠጋግተው ከታሰሩ ቦኋላ እንዲጣበቁ በማድረግ ቀጭንና ወፍራም ድምፅ እንዲፈጥሩ ሆነው የሚዘጋጅ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

### 3.1.2.5 ሁልዱዱዋ



ሁልዱዱዋ አጠር ካለ ቀርካሃና ተለቅ ካለ ከበሬ ቀንድ የሚሰራ ለሃዘን ሥነ ሥርዓት የሚገለገሉበት ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ነው።

### 3.1.2.6 ጨቻ ዝዬ



ጨቻ ዝዬ፡ ከማሽላ አገዳ የሚሰራና በከብት አንጀት የሚሸፈን አራትና ከአራት በላይ ሆነው እየተቀባበሉ የሚጫወቱበት ውዝዋዜ ለማድመቅ የሚያገለግል የሙዚቃ መሣሪያ ነው።

### 3.1.2.7 ዙምባራ (አዋዛ)







ዙምባራ አዋዛ አስራሁለት መሳሪያ ተጫዋቾችን የሚይዝና የሚሰራውም ከቀርከሃ መጠናቸው የተለያየ ቅሎች ተሰንጥቀው ቀርከሃው እንዲለብሳቸው ይደረጋል በመጫውቻው አፍ የተለያዩ ቅርፅ ያላቸው ቅሎች ይደረጋሉ፡፡

### 3.1.3 የምት የሙዚቃ መሣሪያዎች

የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምፃቸው የሚፈጠረው በእጅ ወይም ለዚህ ተብሎ በተሰራ መምቻ እንጨት አማካኝነት ሲመቱ ነው፡፡

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- የምት መሳሪያዎች ድምፃቸው በምት መፈጠሩን ትረዳላችሁ፡፡
- አሰራራቸውን በሚገባ ትረዳላችሁ፡፡

#### 3.1.3.1 ከበሮ



ከበሮ በስተቀኝ ያለው በስተግራ ካለው ሰፋ ያለ ሆኖ ከእንጨት የሚሰራ ከፊትና ከኋላ የከብት ቆዳ ይለብሳል በአብዛኛው በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በዝማሬ ወቅት የሚገለገሉበት መሣሪያ ነው፡፡

### 3.1.3.2 አታሞ



አታሞ አጠር ያለና ከቀኝና ከግራ ተመሳሳይ መጠን ባለው ክፍት እንጨት ወይም ቆርቆሮ የሚሰራና ነው:: ክፍት ቦታው ብቆዳ ይሸፈናል:: አታሞ በተለይም ለአለማዊ ሙዚቃ ለጭፈራ የሚያገለግል መሣሪያ ነው::

### 3.1.3.3. ነጋሪት



ነጋሪት ትልቅ እንጨት ተቦርቡሮ ገበቴ ቅርፅ ከያዘ ቦኃላ የከብት ቆዳ የሚለብስ 1.ትልቁ ደባ 2.አማሪት 3.ጥራን በመባል የሚጠራ ጥንታዊ ከሆኑት አንዱ ሲሆን እንደዛሬው መገናኛ ብዙሃን ከመስፋፋታቸው በፊት የመንግስት የመገናኛ አገልግሎት በሰልፍ ስነስርአት ጊዜ መሳሪያውን በመምታት (በመጎሰም) ይገለገሉበት የነበረ የሙዚቃ መሣሪያነው::

### 3.1.3.4 ጎርባ



ጎርባ ከበሮ ክፍት ከሆነ መጠኑ ረዘም ካለ እንጨት የሚሰራ ከላይ የከብት ቆዳ የሚለብስ ለተጫዋቾች ሁለት መንታ የከበሮ አይነት ነው

## 3.1.4 በእጅ በማነቃነቅ፣ በጣት በመምታትና እርስ በእርስ በማጋጨት ድምፅ የሚያወጡ መሳሪያዎች

### 3.1.4.1 ቶም





ቶም ከእንጨትና ከቸንጥላ ሽቦ የሚሰራ በጋምቤላ ውስጥ ታዋቂና ተወዳጅ የሆነ የሙዚቃ መሣሪያ ነው።

### 3.1.4.2 ፅናፅል






ፅናፅል ባላ ቅርፅ ሲኖረው ከነሃስና ከብር የሚሰራና ድምፅ ሊሰጡ የሚችሉ ትንንሽ ቆርቆሮዋች ገባሉ ለመንፈሳዊ ዝማሬ የሚገለገሉበት መሣሪያ ነው።

### 3.1.4.3 ቃጭል






ቃጭል ፡አብዛኛውን ጊዜ ለመንፈሳዊ ዜማ የሚያገለግል መሣሪያ ነው።

### 3.1.4.4 መቋሚያ



መቋሚያ ለመንፈሳዊ ዝማሬ ከከበሮው ስልት ጋር በተዛመደ ሁኔታ በመንቀሳቀስ የሚገለገሉበት መሣሪያ ነው::

### 3.1.4.5 ቻንቻ



ቻንቻ: ከቆዳ የሚሰራ በጭፈራ ጊዜ በወገብ ላይ የሚታሰር አዳማቂ መሣሪያ ነው::

### 3.1.4.6 ጋሬ



ጋሬ: በእግር ላይ ታስሮ ጭፈራን የሚያደምቅ የሙዚቃ መሣሪያ ነው::

**መልመጃ**

I. ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

_______1. ከማሽላ አገዳ የሚሰራ የትንፋሽ መሳሪያ የቱ ነዉ?

ሀ. ዋሽንት ለ. ጪቻ ዝዩ ሐ. ዋዛ መ. እምቢልታ

_______2. አስራ ሁለት ተጫዋቾች አባላት ያሉት ከቀርከሃ የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ የቱ ነው?

ሀ. ከበሮ ለ. ድንኬ ሐ. ዙምባራ መ. ለናሐ

_______3. ከአጫጭርና ቀጫጭን ሸንበቆዎች የሚሰራ የትንፋሽ መሳሪያ የቱ ነዉ?

ሀ. ፋንፋ ለ. መለከት ሐ. ሁሉዱዱዋ መ. ጋሬ

________4. የመሰንቆ ክር የሚሰራው ከምንድን ነዉ?
ሀ. ከጅማት ለ. ከፕላስቲክ ክር ሐ. ከፈረስ ጭራ መ. ከከብት ጭራ

________5. የክር መሳሪያዎችን ሁለቱን ምሶሶዎች የሚያገናኘው አካል የቱ ነው?
ሀ. ብርኩማ ለ. ገበቴ ሐ. ቀምበር መ. መቃኛ

II. ከዙበታች በሀ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በለ ስር ካሉት መልሶች ጋር አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ___ 1. ድርድር | ሀ. የድምፅ ሳጥን |
| ___ 2. ፒክአፕ | ለ. በስፒከር ድምፅ የሚያጎላ |
| ___ 3. የክር መሳሪያን ድምፅ የሚያጎላ | ሐ. ድፍን፣ አውራ ፣ይማ |
| ___ 4. የእምቢልታ ክፍሎች | መ. መለከት |
| ___ 5. የድምፅ ማውጫው የዋንጫ ቅርፅ ያለው | ሠ. የበገና አጨዋወት |

III. ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች ዓ/ነገሮች ትክክል ከሆነ ዕውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱን ጻፉ።

________1. ነጋሪት ለአለማዊ ሙዚቃ ብቻ የሚያገለግል መሣሪያ ነው።
________2. ቶም መጫውቻ ቁልፉ ከዣንጥላ ሽቦ ይሰራል።
________3. ዋሽንት ከቀርከሃ የሚሰራ በላአራት ቀዳዳ የትንፋሽ መሳሪያ ነው።
________4. የመሰንቆ (መምቻ) መጫወቻ ደጋን ቅርፅ አለው።
________5. አታሞ በጥንት ጊዜ መልዕክት ማስተላለፊያ መሳሪያ ነበር።

## 3.2. የህገረሰብ ውዜዋዜዎች

ስልቶች

የውዝዋዜ ስልቶቻችን በየብሔር ብሔረሰቦች ባህል መሰረት የሚከወን ነው። በዚህም መሰረት በየክልሎች ያሉትን የውዝዋዜ አይነቶች በቪዲዮ በታገዘ ከሙዚቃው ጋር በአንድነት ተማሪዎች እንድትሰሩ ይጠበቃል።



# 6ተኛ ክፍል

## የክወና እና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## ምዕራፍ ሶስት ታሪካዊና ባህላዊ አግባብ/አውድ





**ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለ ተራኪ ምንነት ትረዳላችሁ::
- ትረካ አንፃሮች ታውቃላችሁ::
- አጭር ልቦለድ ትተርካላችሁ::
- በምን አንፃር እንደ ቀረበ ትናገራላችሁ::
- ታሪኩን በቪዲዮ ቀርጻችሁ ታቀርባላችሁ::

ስለ ታሪክ ምንነት እና በምን በምን ሊቀርብ እንደሚችል በአምስተኛ ክፍል ትምህርታችሁ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ታሪኩ ተመስርቶ ስለሚቀርብበት ተራኪ ምንነትና የትረካ አተራረክ ዘዴዎች (አንፃሮች) እናያለን፡፡

እያንዳንዱ ታሪክ ነጋሪ ወይም ደራሲ ታሪኩን ለአንባቢ (ተደራሲ) የሚያቀርበው ህዝቡን ያስደስታል የፈለኩትን ማህበራዊ ጉዳይ ያሳይልኛል ብሎ በሚመርጠው ዘዴ ነው፡፡ ታሪኩ በየትኛው ዘዴ ይተረክ፤ እንዴትስ መሳጭ በሆነ መልኩ ቀርቦ ሳቢ ይሁን በማለት በተለያዩ ፍሬ ነገሮች በማቀናጀት ያቀርባል፡፡

<u>ተራኪ</u>፡- በታሪክ ፈጣሪው (ደራሲው) እና በተደራሲው መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚተረጉምና የሚገልፅ፤ አልፎ አልፎ በግልፅ አብዛኛውን ጊዜ ግን በታሪኩ ውስጥ ሆኖ በውስጥ አዋቂነት የሚኖር፤ የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚያቀርብልን ነው፡፡ ስለዚህ ተራኪ ታሪኩ የሚመለከተው ተሳታፊ ወይም ታሪኩ የማይመለከተው ታዛቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ታሪኩ የሚመለከተው ተሳታፊ ከሆነ የራሱንም ሆነ ከእሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ባለታሪኮች

(ገፀ- ባህርያት) ታሪክ በእሱው እይታ አመለካከት ያቀርባል፡፡ ታዛቢ ከሆነ ደግሞ ከታሪኩ ውጪ በመሆን ዳር ቆሞ ያየውንና የታዘበውን ያቀርባል፡፡ አንዳንዴ ታሪኩ ውስጥ ያሉትን ባለታሪኮች የተወሰነ ብቻ እውቀት ሲኖረው ሁሉንም ነገር በግልፅ ለማቅረብ አይችልም፡፡ ሁሉንም አይነት ነገር አወቂ ሆኖ ሲቀርብ ደግሞ ስለታሪኩ ባለቤቶችም ሆነ ስለገቡባቸው ሁኔታዎች በግልጽ በማቅረብ ፍርድ እና አስተያየት መስጠትም ይችላል፡፡ እንዲሁም በታሪኩ ገፀ- ባህርያት መካከል ጣልቃ ሳይገባ ራሳቸው ማንነታቸውን በንግግራቸውና ድርጊታቸው እንዲገልፁ እድል ይሰጣል፡፡

ስለዚህ የተራኪውን አንፃሮች ስናይ በሚከተሉት መልኩ ቀርቦ እናገኘዋለን፡

<u>ሁሉን አወቅ</u>፡- ስለሚከዎነው ድርጊት ምንነትና ስለገፀ- ባህርያቱ ሁሉንም ነገር ስለሚያውቅ በመተቸት እና አስተያየት በመስጠት ጭምር ተንትኖ ያቀርባል፡፡

<u>ዉሱን ሁሉን አወቅ</u>፡- ዋናውን ገፀ- ባህርይ እየተከተለ ከእሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ባለታሪኮች ጭምር ከዋናው ገፀ- ባህርይ አንፃር ያቀርባል፡፡

<u>አንደኛ መደብ ተራኪ</u>፡- የታሪኩ ተሳታፊ በመሆን እንዳየሁት፣ እንደደረሰብኝ.... እያለ ያቀርባል፡፡

<u>ተውኔታዊ</u>፡- ለባለታሪኮቹ ነፃነት በመስጠት ስለራሳቸው እንዲገልፁ እድል የሚሰጥ ሲሆን ዳር ሆኖ በመታዘብ ግልፅ ያልሆኑትን ነገሮች ብቻ ይተርካል፡፡

**መልመጃ 1**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች አዛመዱ**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. ተውኔታዊ የትረካ አንፃር | ሀ. እኔ እያለ ያቀርባል |
| 2. አንደኛ መደብ የትረካ አንፃር | ለ. ፍርድና ሳይቀር ይሰጥበታል |
| 3. ደራሲውንና ተደራሲውን ያገናኛል | ሐ. ዳር ሆኖ ይታዘብበታል |
| 4. ሁሉን አወቅ የትረካ አንፃር | መ. ሰዓሊ |
| | ሠ. ተራኪ |

**የሚቀጥለውን በፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር ታትሞ ከቀረበው የአጫጭር ልቦለዶች ታሪክ ውስጥ በበውቀቱ ስዩም የተደረሰውን ወዝቶች እስኪሞሉ የተሰኘ አጭር ታሪክ አንብቡና ቀጥሎ ለሚቀርቡት የመልመጃ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡**

ስለምትኬ ለመፃፍ ካሰብኩ ብዙ ጊዜ ሆነኝ፡፡ ግን ከየት እንደምጀምር አላውቅም፡፡

... ምትኬ ወንቃ ጊዮርጊስ ተወለደ፡፡ ዕድሜው ለንባብ ሲደርስ ደብረማርቆስ ወርዶ ተማረ፤ ከዕለታት አንድ ቀን አዲስ አበባ ሄደ፡፡ ከዚያም ሎተሪ ያዞር ነበር፡፡ ምትኬ ለወላጆቹ የመጀመሪያ ልጅ ነው፡፡

ብዬ ልጀምር እፈልግና በራሴ አፃፃፍ አፍራለሁ፡፡ የፃፍኩትን ደግሜ ሳነበው አስቀባሪዎች በቀብር ጊዜ ከሚያነቡት የሟች ማስታወሻ ጋር ይመሳሰልብኛል፡፡

ምትኬ ግን አልሞተም፡፡ ወደፊትም የሚሞት አይመስልም፡፡ አዲስ አበባ መጥቶ ከብዙ ርሀብ መንጋጋ፣ ከብዙ ማጅራት መቺ መዳፍ፣ ከብዙ የፈጣን መኪና አምልጧል፡፡

ሊቁ ተዋነይ የዕፀ ህይወትን ቅጠል ያገረሰው ይመስል በሞት ጥላ መካከል ያለ ፍርሀት ተመላልሷል፡፡ ስለዚህ የሙት ማስታወሻ በመሰለ መግለጫ የምትኬን ታሪክ መናገር ፍርደ ገምድልነት ነው፡፡

ታዲያ ምን ብዬ ልጀምር?

…ቀጭን፣ ጎበጥ ያለነው፣ ትቢያ የቃመ ፊቱንና ቅጥነቱን አስተባብረን ብንመለከት ምትኬ እግዜር አዳምን ከመሳሉ በፊት ያወጣው ንድፍ ይመስላል፡፡

ይሄን ከፃፍኩ በኋላ የበለጠ አፈርኩ፡፡ በርግጥ አፃፃፌ ትክክለኛውን የምትኬን የሰውነት ገፅታ ይገልጣል፤ ቢሆንም ግን ላንባቢው የሚፈይድለት ምንም ነገር የለም፡፡ ምትኬ ሎተሪ አዟሪ እንጂ ሞዴሊስት አይደለም፡፡ ስለዚህ በሰውነት አቋሙ መዳኘት ልክ አይደለም፤ ምትኬ ምን ቢቀጥን ሎተሪ የሚያዞር መዳፍ አለው፡፡

በዚያ መዳፍ ውስጥ ደግሞ ሁላችንንም ከትቢያ ወደ ሰገነት ሊያወጣን የሚችል ዕድል ተሸሽጓል፡፡

… ምትኬ ወደ አዲስ አበባ ከመምጣቱ በፊት የስድስተኛ ክፍል ትምህርቱን በሁለተኝነት አጠናቋል፡፡

ይሄ ሀቅ ነው፡፡ ግን ታሪክ ለመጀመር የሚያበቃ አንቀፅ አይደለም፡፡ እንዲያውም የምትኬን ታሪክ ወደ ስራ ማመልከቻነት ዝቅ ማድረግ ነው፡፡

እስከ ስድስተኛ ክፍል መማሩ፤ ከክፍል ሁለተኛ መውጣቱ፣ ለአዲስ አበባ ህይወቱ የጠቀመው ምንድን ነው? ምናልባት የሎተሪ ቁጥሮችን ማንበብ፡፡

አዎ ከክፍል ሁለተኛ መውጣቱ፣ ለአዲስ አበባ ህይወቱ የጠቀመው ምንድን ነው? ልክ ነው ስድስት ዓመታት ሙሉ ወደ ተማሪ ቤት የተመለሰው ጥቂት ብርሀን ብዙ ጭስ የሚተፋ ኩራዝ ያጠናው ሎተሪ ቁጥር ለማንበብ ነው፡፡

… ምትኬ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ወዛም ሽመል እና አረንጓዴ መጎናፀፊያ ብቻ ይዞ ነው፡፡

ብዬ ለመጀመርም አስቤ ነበር፡፡ ግን ይሄ የምትኬ ብቻ ሳይሆን የጓደኞቹ ሁሉ የጋራ መገለጫ ነው፡፡

ሽመላቸው ከምንም አያስጥላቸው፤ አረንጓዴ መጎናፀፊያቸው ከማንም አይቀላቅላቸው፡፡ ምትኬ በዚህ ረገድ ከጓደኞቹ ጋር አንድ ነው፡፡

ጓደኞቹም እሱም አረንጓዴ መጎናፀፊያ ለብሰውና ላብ ያወዛው ሽመል ይዘው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ሲሳይ ፍለጋ ነው፡፡ ሰርተው ገንዘብ ቋጥረው ለመመለስ ፈልገው ነው፡፡ እንደ ገባር ጅረት የቋጠሩትን ይዘው ወደ ሸለቆዎች ወደ ግዙፍ ወንዞች ለመፍሰስ ተመኝተው ነው፡፡

የምትኬን ታሪክ በምን በኩል በየት በኩል እንደምጀምረው ለብዙ ጊዜ ግራ ሲገባኝ ቆይቷል እናም ለረጅም ጊዜ ጢማም አገጩን መዳፌ ላይ ጥዬ አሰላስለዋለሁ፡፡

አሰላስዬ፣ አሰላስዬ ከዕለታት አንድ ቀን የተሻለ ጅማሬ መጣልኝ፡፡ ለምን ከቃለምልልሱ

አልጀምርም ብዬ አሰብኩ፡፡ ምትኬ ቃለምልልሱን ያደረገው ከጋዜጠኛ ጋር አይደለም፡፡ ጠጅ ቤት በር ላይ ግዙፍ ጫማቸውን ከሚያስወለውሉት አዛውንት ጋር ነው፡፡

ወዲህ ና እስቲ ሸበላው! አሉት፡፡

መጣ፡፡

ስምህ ማን ነው? አሉት፡፡

ነገራቸው፡፡

የማን ምትክ ነህ?

አቀርቅሮ ዝም አለ፡፡

አመጣጥህ ከየት ነው?

ተጎጃም!

ከጎጃምማ ከጎጃም ነው፤ መቼም ከኮሪያ አትመጣ! እንዲያው ልዩ ስፍራውን አልኩህ እንጅ?

ገጠር ነው አላቸው፡፡

የገጠሩ ስም የለውም?

ስም የሌለው አገርማ የለም አብዬ፡፡

እኮ ስሙ ማን ነው?

ወንቃ!

የትነው እሱ ደሞ?

ተማርቆስ ፈንጠር ብሎ፡፡

ሊስትሮው ሳጥኑን በቡርሽ ሲወቅረው መጀመሪያ እግራቸውን ቀጥለው ጥያቄያቸውን ቀየሩ፡፡

ምንድን ነው የምትሰራው?

የቀን ስራ ነው አብዬ፡፡

የቀን ስራማ የቀን ስራ ነው መቼም ፓርላማ አትቀመጥ... የስራውን ልዩ ስም አልኩህ እንጂ!

ሎተሪ አዞራለሁ!

ምን ሎተሪ ታዞራለህ፤ ሎተሪ ያዞርሃል እንጅ አሉት፡፡

የሚጠይቁት መልስ ለማግኘት ፈልገው እንዳልሆነ ገባው፡፡ ከጥያቄያቸው በፊት መልሱን ያውቁታል፡፡ እና ሊጨቁኑት ከባድ ተረከዝ ባለው ጫማቸው እንደ ሊስትሮው ሳጥን እያፈራረቁ ሊረግጡት እንደ ጠሩት አወቀ፡፡

ከመጣህ ስንት ወር ሞላህ?

ከነገ ወዲያ ድፍን ሶስት ወር ይሞላኛል፡፡

መች ነው ወደ ሀገርህ የምትመለሰው?

ይህንን ጥያቄ ብዙ ጊዜ ተጠይቋል፡፡ አዲስ አበባ ከሁሉም አገር፤ ከሁሉም ከተማ፤ ከሁሉም ህዝብ የተውጣጡ ሰዎች ይኖሩባታል፡፡ ሁሉም ግን ባለባበስ ተመሳስለዋል፡፡

በቦላሌ አንድ ሁነዋል፡፡
ስለዚህ እርስ በርሳቸው መች ነው ወደ አገርህ የምትመለሰው? አይባባሉም፡፡ይህ ጥያቄ እንደ ዱብዕዳ ድንገት የሚወርድባቸው ባለባበስ የተለዩት ናቸው፡፡ አዲስ አበባ ለቁምጣ፣ ለሽመልና ለንቃቃታም እግር ዕውቅና አትሰጥም፡፡
አዲስ አበባ ቁምጣ ታጥቀው አረንጓዴ መጎናፀፊያ ጠምጥመው የመጡ ጎረምሶችን የምትቀበላቸው ፊቷን አጨፍግጋ ነው፡፡ ሁሉንም በጅምላ የቆሎ ተማሪ ብላ ትጠራቸዋለች፡፡ በልመናቸው ብቻ ታስታውሳቸዋለች፡፡ እስካሁን ለዩኒቨርሲቲ ተማሪወች እንጅ ለቆሎ ተማሪዎች የምትራራበት ምክንያት አላገኘችም፡፡
በቆሎ ተማሪዎችና በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል የዕውቀትና የአኗኗር ልዩነት አለ፡፡ እንደኔ አራት አመታት ተምሮ፣ ጥቂት የሥነ- ፅሁፍ ህግጋት በማወቅ ትምህርቱን የደመደመ ሰው፣ የዜማ፣ የቅኔና የመፃህፍት አገባብ ዕወቀት ካለው የቆሎ ተማሪ በማዕረግ እንደማይበልጥ ይገባዋል፡፡ ስለዚህ ሌላ ልዩነት ይፈልጋል፡፡
የአኗኗር
የቆሎ ተማሪዎች የሚኖሩት በላባቸው በሚያገኙት ሳይሆን በየደጁ ቆመው በሚሰፈርላቸው ቀለብ ነው፡፡ የዩንቨርሲቲ ተማሪዎችም ይህንን ነው የሚያደርጉት፤ መቼም፣ ከሌክቸር በኋላ ድንጋይ የሚፈልጥ፣ ታክሲ የሚነዳ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የለም፡፡ ይልቅ ከሌክቸር በኋላ ሌሎች የሚሰፍሩለትን ቀለብ ተሰልፎ ይወስዳል፡፡
ልዩነቱ ይሄ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ከሆንክ ሌሎች የሚሰፍሩልህን ቀለብ ከወሰድክ ከፍቴሪያ ገብተሀል! የቆሎ ተማሪ ከሆንክ ሌሎች የሚሰፍሩልህን ቀለብ ከወሰድክ ለምነሀል! አዲስ አበባ ሰዎችን በልብሳቸው ልዩነት እንጂ በልባቸው ታላቅነት አትዳኝም፡፡ ምትኬ በአዲስ አበባ አይን የማይመረመር ልብ አለው፤ በዚያ ልቡ ውስጥ ብዙ
ምስጢር፤ ብዙ እንቆቅሽ አለ፡፡ ከእንቆቅልሾቹ አንዱ ደግሞ ጫማ የሚያስቀቡት አዛውንት የጠየቁት ጥያቄ ነው፡፡
መች ነው ወደ አገርህ የምትመለሰው?
የዛሬ ሁለት ወር ግድም አባቱ በስልክ ያነሱለት ጥያቄም ይሄ ነበር፡፡
መች ነው ወደአገርህ የምትመለሰው? በርግጥም መች ነው ወደ አገሩ የሚመለሰው? አዲስ አበባ በመጣ በወሩ ሎተሪ ሸጦ አምሳ ብር አጠራቀመ፡፡
አምሳ ብሩን ለደብተር፣ ለሸራ ጫማ፣ ለተማሪ ቤት ክፍያ፣ ለትራንስፖርት ሸንሽኖ በሃሳቡ ከመደበው በኋላ ለመመለስ ተሰናዳ፡፡
ከዚያ እየመጣ መሆኑን ለማሳወቅ ስልክ ደወለ፡፡ በየሰንበቱ አባቱ ከወንቃ ወደ ማርቆስ ተጉዘው ወንድማቸው ቤት የሚመጡት የልጃቸውን ድምፅ ለመስማት ነው፡፡
ስለቤቱ፣ ስለከብቱ ጤንነት ከነገሩት በኋላ መች ነው ወደ አገርህ የምትመለሰው? አሉት፡፡
ተነገ ወዲያ እመለሳለሁ! አላቸው፡፡
ወንድምህ ሳይቀድምህ ትመለሳለሀ? አሉት፡፡
ኸትኛው(የትኛው) ወንድሜ?

ይሽ መጨው፣ እናትህ ሆድ ወስጥ ያለው! አሉት እየሳቁ፡፡
መውለጃዋ(መውለጃዋ) ደረሰንዴ?
አዎ ተአንድ ሳምንት በላይ አትሽድም!
እንዳሰበው በሁለት ቀናት ውስጥ አገሩ አልተመለሰም፡፡ ጥቂት ተጨማሪ ገንዘብ ማግኘት እንዳለበት አመነ፣ ስለዚህ አስራ አምስት ቀን ጨመረ፡፡
አስራምስት ቀን ሲያልቅ ሎተሪ ያፈራለትን ይዞ መርካቶ ወረደ፡፡
እስቲ ለህጣን ልጅ የሚሆን ልብስና ፎጣ አሳዩኝ አላቸው ግማሽ ሰዓት ተከራክሮ ወይባ ቀለም ያለው ፎጣ፣ የልጅ ሱሪና ሹራብ ከነቀቡ ሸመተ፡፡ ራቁቱን የመጣ ወንድሙን በባዶ እጁ እንደማይቀበለው አመነ፡፡
ቀጥሎ ምን ይቀራል
መሄድ ብቻ፣
ግን ከመሄዱ አስቀድሞ እንደልማዱ ስልክ መታ፣
የኔ ልጅ!
ደህና ነህ አባባ?
ደህና ነኝ በደህና ነው እልም ብለህ የቀረህ ልጄ?
ደህና ነኝ ትንሽ አልሞላልህ ብሎኝ ነው!
አሁን መቼ ትመለሳለህ?
ተነገ ወዲያ መጣለሁ!
እሰይ እናትህም በሰላም ተገላገላች!
ወንድ ነው ሴት?
ሁለቱም ወንድ ናቸው ልጄ
ሁለቱም!!!
አዎ መንታ ናቸው እግዜር ይመስገን፡፡
ስልኩን ሲዘጋ እንደ ቆረበ ብላቴና ለረጅም ጊዜ አፉን ከድኖ ጭጭ አለ፡፡
ላንዱ ህፃን ብቻ ልብስ ገዝቶ ወደ አገሩ ሲመለስ ሊደርስበት የሚችለውን ዘበት ሲያስበው ደነገጠ፡፡ ስለዚህ ጥቂት ጊዜያትን ለመታገስ ቀረጠ፡፡ ቆየ፣ ምን ሲያደርግ ቆየ
ሲሰራ ወይስ ሲለምን
ይሄንን በርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም፡፡
በዩንቨርሲቲ ተማሪዎችና በቆሎ ተማሪዎች መካከል የተሰወረ አንድነት እንዳለ ሁሉ በመስራትና በመለመን መካከል የጋራ ርስት አለ፡፡
ምትኬ ወደ አዲስ አበባ ከመምጣቱ ሁለት ቀን አስቀድሞ ወደ መኝታ ክፍላቸው ጠርተው አስጠነቀቁት አደራ ልጄ! በላብህ አንጅ በተማጽኖ እንዳትኖር አሉት፡፡ ምትኬ ሎተሪ ማዞር ሲጀምር ከንጉስና ካውራ ደሮ የማይተናነስ ኩራት ተሰማው፡፡
ሎተሪ አዟሪነት አባቱ ከሚጠሉት ከልመና ፍፁም ተቃራኒ ሆኖ አገኘው፡፡ የልመና አላማ ሳይለፉ ሳይደክሙ ከአዲስ አበባ ሰዎች ሲሳይ መቀበል ነው፡፡ የሎተሪ ማዞር አላማ ግን

የአዲስ አበባ ሰዎች ያልደከሙበትን ሲሳይ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡
ምትኬ ሎተሪ ባዞረ ቁጥር ሰዎች ቁምጣ የለበሰ ሃብት አድርገው እንደ ሚያስቡት ሚሰማው ለዚህ ነው፡፡ ያለዚህ ስሜት ብዙም መከራዎችን መርሳት አይችልም ነበር፡፡ እየቆየ እየሰነበተ ግን የአዲስ አበባ ህዝብ ሎተሪ በመቁረጥ እንደማይተዳደር አወቀ ይህ ማለት ለአዟሪዎች አይገደውም ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ደንበኞች ሲያገኙት ስማ አንተ! ሰባት ጊዜ ቆርጬ ያልደረሰኝ ምን አይነት ጎደሎ ብትሆን ነው! ይሉታል፡፡
ሰዎች በእድላቸው ተስፋ ላለመቁረጥ የሚወስዱት የመጨረሻ አማራጭ ዕጣ ያቀበላቸውን ዕጅ መርገም ነው፡፡ እድላችንን ለሌሎች ማጋራት የምንፈቅደው እድለ ቢስ የሆንን እለት ብቻ ነው፡፡
ምትኬ ከእለታት አንድ ቀን ከመጤፍ ሳይቆጥሩት የሚያልፉትን አልፎ ሂያጆች ባካችሁ ሎተሪ ግዙኝ! ሎተሪ! ብሎ ሲል ራሱን አገኘው፡፡
ባካችሁ ሎተሪ ግዙኝ! የሰራተኞች ሳይሆን የተማፃኞች ድምፅ ነው፡፡ ስለዚህ በመለመን እና በመስራት መካከል ያለው አጥር ድንገት ሲፈርስ ተሰማው፡፡ አባቱን ለማስደሰት ገንዘብ ይፈልጋል፤ አባቱን ለማስደሰት ባካችሁ ሎተሪ ግዙኝ ይላል! ሎተሪ ብሎ ተማጸነ፡፡ አባቱን ለማስደሰት አባቱ ወደ ፈሩት ምዕራፍ ተጠጋ፡፡
በዚህ አይነት ሁለት ሰንበት ጨመረ፤ ግን እንደድሮው አልቀናውም እና በልቡ ለካ የሰው እንጂ የእድል መንትያ የለውም! አለ፡፡
ግን ጥርሱን ነከሰ፡፡
ልቡን አጠነከረ፡፡
ለወንድሙም፣ ለመንትያ ወንድሙም ልብስ ሳይዝ እንደማይመለስ ለራሱ ወሰነ፡፡
ሶስት ወር ሞላው፡፡
ክረምቱ መጣ፡፡
የትምህርት መመዝገቢያ ቀን አለፈ ከሳምንት አንዴ ይደውል የነበረውን ስልክ ርግፍ አድርጎ ተወው፡፡
እየቆየ፣ እየሰነበተ፣ እየከረመ የሰፈሩ፣ ያገሩ መልክ ከፊቱ ላይ ተደመሰሰበት፡፡ ወንቃና ማርቆስ እንደ አትላንቲክ ከሌላው ምድር ተነጥለው ሰጠሙ፡፡ ከሌላው አፈር ተለይተው ሚሙ፡፡
ካዛውንቱ እግር ስር ያለው ሊስትሮ ሳጥኑን በቡርሽ ደግሞ ወቀረው፡፡ ምትኬ ከሃሳቡ፣ አዛውንቱ ከማናውቀው ትዝታቸው ባነኑ፡፡
መቼ ነው የምመለስ ያልከኝ አሉት፡፡
እኔ እንጃ! አላቸው፡፡
በትዝታ ሲያዩት ከቆዩ በኋላ ተረት ልንገርህ አሉት፡፡
ቀና ብሎ አይቷቸው ዝም አለ፡፡
አንድ ጊዜ አንበሳ ታመመና አንስሳት ሁሉ እየመጡ ይጠይቁታል፡፡ ሲጠይቁት፣ ሲጠይቁት ቆዩና ቀበሮ በተራዋ መጣች፡፡

እሽ! አለ ሊስትሮው፡፡
ቀበሮ ከዋሻው አፍ ራቅ ብላ ቁማ፣ እግዜር ይማርህ አለችው፡፡ አንበሴ ይህኔ በቁጭት ምነው ገብተሽ አትጠይቂኝምን ይላታል፡፡ ይሄኔ አዬ ብገባ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ግን ወደ ዋሻው አፍ የሚሄዱ ዱካዎችን እንጂ የሚመለሱትን አላየሁም! አለችው፡፡ አይ ቀበሮ ጥበቧ ስፍር የለው!
አዛውንቱ ተረቱን ፈጽመው ለሊስትሮው ሽልንግ ከፍለው ሄዱ፡፡
በተወለወለ ጫማቸው መንገዱ ላይ ግዙፍ ዱካቸውን እያተሙ ርቀው ሄዱ፡፡
ጥቂት ቆይቶ ከዱካቸው አጠገብ ምትኬ የንቃቃታም እግሩን ዱካ ያስቀምጣል፤ ይሄዳል፣ ይዞራል፤ ሎተሪ ያዞራል፡፡
ቆይቶ ቆይቶ፣ አዲስ አበባ ያንበሳው ዋሻ እንደሆነች ገባው፡፡ አቧራ ላይ ያሉት ዱካዎች መግባት እንጅ መመለስን አያሳዩምና፡፡

**የመልመጃ 2**

**የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ምትኬ ጎበዝ ተማሪ ነበር፡፡
2. ምትኬ ወደ ሃገሩ እንዳይመለስ ያደረገው ስለተመቸው ነው፡፡
3. ምትኬ መንትያ ወንድሞቹን አይወዳቸውም፡፡
4. አዲስ አበባ ለኗሪዎቿ ፍትሃዊ አቀባበል የላትም፡፡
5. ተራኪው ከመጤፍ ሳይቆጥሩት ሲል ጉዳዬ ብለው ሳያዩት ማለቱ ነው፡፡

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ**

1. ታሪኩ የቀረበባቸው አንፃሮች ምን ምን ናቸው?
2. የታሪኩ ዋና ገፀ- ባህርይ ማነው?
3. የታሪኩ ባለቤት ዓላማ ምንድን ነው?
4. ተራኪው ሊነግረን የፈለገው ቁም ነገር ምንድን ነው?

ባብ/አውድ

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የዕይታ ጥበብ ታሪክ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ያደብራሉ::
- በዕይታ ጥበብ ታሪኮችን በንድፍና በቀለም ቅብ ያዳብራሉ::
- በዕይታ ጥበብ ውጤቶች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ሀገርኛ ታሪኮችን በስዕላዊ ማብራሪያ ይገነዘባሉ::
- የተደገፉ ኢትዮጵያዊ በሆነ ገላጭ በስዕል ወይም በፎቶበማስተማር::
- የማድነቅ፣ የመሣተፍና የመንከባከብ ፍላጎታቸው ይጨምራል::
- የዕይታ  ጥበብና ውጤቶች ለአንድ ማህበረሰብ የባህል ፣ የማንነትና የአስተሳሰብ ነፅ ብራቅ መሆናቸውን ይገነዘባሉ::
- የዕይታ ጥበብ ውጤቶች በማህበረሰብ ታሪክ ዉስጥ ያላቸው ፋይዳ ይገነዘባሉ::
- የኢትዮጵያን ዕይታዊ ጥበብ ታሪክ ለማወቅ ቆየት ያሉ የተረሱ ታሪኮችን አለባበስ ማዕረግ በቀላሉ ይተዋወቃሉ::

**የቀድሞ ዘመን የሹመት ማዕረግ**

1- ንጉሠ ነገሥት
2- ንጉሡ
3- መርዕድ አዝማች
4- ዋግሹም
5- ራስ ቢት ወደድ
6- ጃንጥራር
7- ሊጋባ ደጃዝማች
8- ጸሐፊ ትእዛዝ
9- አዛዥ
10- ባጅሮንድ ................. ወዘተ

## ሊጋባ/ ዳጃዝማች /

ሊጋባ የቤተ መንግስት አገልጋይ ማዕረግ ነው:: የስራ ድርሻውም ንጉሡን ለማነጋገር የሚሹ ሰዎችን በሰርዓት ንጉሱ ዘንድ ማቅረብ ሲሆን አጋፋሪው የሊጋባው ረዳት ሆኖ ሰራውን ያቀላጥፋል።

አንዳንድ መዝገቦች ሊገባን የቤተመንግስቱ የስራ ቤት አለቃ እንደሆነ አድርገው ቢገልጹም የሊጋባ ዋነኛ ተግባራት የተለያዩ ጉዳይ ንጉሡን ለማነጋገር የሚመጡ ሰዎችን ጉዳያቸው መሰረትና በደረጃቸው ንጉሱ ዘንድ ማቅረብ እና የተለያዩ የቤተ መንግስት ፕሮግራሞች ሲኖሩ ስራአቱን ማስተባበር ነው ::



ሥዕል፡- የሊጋባው ባለጉዳዮችን ከንጉሱ ፊትሲያቀርብ

ምንም እንኳን የሊጋባ ማረግ እና ተግባር የቤተመንግስት ስራአት የሚያትት ስርአተ ግብር ስርዓተ መንግስት በተሰኙ መዝገቦች ውስጥ ባይካተትም አሉ ነገር ግን የሊጋባ አገልግሎት በደንብ ጎልቶ የወጣው 17ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን በተለይም በጎንደር ዘመነ መንግስት ነው:: አፄ ሲሲኒዎስ የሊጋባ ዘድንግል የተባለ አገልጋይ ነበራቸው አጼ ባካፋ ዘመን መንግስትን እንዲሁ ሊጋባ ወልደ ጊዮርጊስና ሊጋባ ዳዊት የተባሉ የቤተመንግስት አገልጋዮች ነበሩ:: ሊጋባዎች የሚሾሙት በእራሱ በንጉስ ሲሆን በጣም ታማኝ የሆኑ ሰዎች ናቸው:: ለዚህ ቦታ የሚመረጡት:: በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቤተ-መንግስት ወሳኝ ከነበሩ ማረጎች መካከል ሊገባ አንዱ ነበር:: አፄ ምኒልክ ገና የሸዋ ንጉስ ሳሉ ሰራዊቱ የሚባል ሊጋባ ነበራቸው:: ይህም የሚኒሊክ የመጀመሪያው ሊገባ ነዉ:: የሊጋባ ክብር ( ማዕረግ ) ከደጃዝማች በታች ሲሆን አንዳንዴም ዳጃዝማቾች ሊጋባነትን ይሾሙ ነበር:: ምንም እንኳን ሊጋባነት የቤተመንግስት ማዕረግ ቢሆንም ጦርነቶች በሚኖሩ ጊዜ በጦር ሜዳ ጦር መርተው ይስለፉም ነበር::



ይህን በተመለከተ”ዝክረ ነገር” ላይ የሰፈረው ጸሁፍ እንደሚከተለው ነው::

ይህ የማዕረግ ስም ንጉሡ ነገሰቱ ዋነኛው ደጅ አጋፋሪ የሚጠራበት ነው:: ከጦር ሚኒስቴሩ በታች ሆኖ ሰው ማስገባትና ማስወጣት ማናቸውንም የጦር አለቃ ራስም ቢሆን እያዘዘ የመንግስቱን ሥራ ማስራት ነው ከዚህምሌላ ወታደር ተበደልኩ ብሎ ሲጮኽለት ልዩነት ሳያደርግ ማናቸውንም የጦር አለቃ በስልጣኑ ይደኛል ፣ ስለዚህም አንዳንድ ጊዜ ከሊጋባው በላይ ታላቅ ማዕረግና ክብር ያላቸው እየተመረጡ ይሾማሉ (በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት በሊጋባ ወልደ ገብርኤል ላይ በደጃ አጋፋሪነቱ ሥራ ደጃዝማች ልዑል ሰገድ መሾማቸውን እናስታውሳለን)::





ራስ ልዑል ሰገድ ምንም በደጃዝማችነት ስም ቢጠሩም በዚያ ጊዜ የበለጠ ክብር እንደነበራቸው ሽማግሌዎች ያረጋግጣሉ:: ይህ የሊጋባነት ስም የሚሰጠው የንጉስ ነገስትና የንጉስ ዋና ደጅ አጋፋሪ ለሆኑት ብቻ ነው፣ሌላው የሻለቃ ግን አጋፋሪውን በዚህ አይነት ስም አይጠራውም:: የንጉሰ ነገስት ሊጋባ ክብሩ እንደ ደጃዝማቾች ያለ ነው፤ይህነንም ሥራ ለቆ ከፍ ብሎ ሲሾም ደጃዝማች ይባላል ::

ምንጭ ፦ ዝክረ ነገር \

**መልመጃ 1፡-**

**የሚከተሉት ለመምህራችሁ በንድፍ ሰርታቹ አሳዩ፡፡**

1. ንጉሠ ነገሥት  2.ንጉሡ  3. መርዕድ አዝማች  4.ዋግሹም
5. ራስቢትወደድ  6. ጃንጥራር  7.ሊጋባዳጃዝማች

**መልመጃ 2፡-**

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡**

1. ሊጋባ የቤተመንግስት አገልጋይ ማዕረግ ነው፡፡
2. ሊጋባ የቤተመንግስት ፕሮግራሞች ሲኖሩ ስራአቱን ማስተባበር ነው ::
3. የሊጋባ አገልግሎት በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት የጀመረ እንደሆነ ይነገራል፡፡
4. አፄ ምኒልክ ገና የሸዋ ንጉስ ሳሉ ሰራዊቱ የሚባል ሊጋባ ነበራቸው ::

መልመጃ 3፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባያችሁት የመስመር ባህሪያት መሰረት በቃላችሁ መልሱ::

1. የቤተመንግስት ማዕረግ ምንድ ነው?
2. አጼ ባካፋ ዘመን መንግስትን እንዲሁ ሊጋባ --------------------ነው?
3. የሊጋባ ክብር (ማዕረግ) ስንትነው?

ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ ላይ ያሉ በቅደም ተከተል የቀረቡ ሲሆንበ‹‹ለ›› ጋር በማዛመድ መልሱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሊጋባ ወልደ ገብርኤል | ሀ. በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት |
| 2. የሊጋባ ዘድንግል | ለ. አጼ ባካፋ ዘመን መንግስትን |
| 3. ሰራዊቱ ሊጋባ | ሐ. አፄ ሲሲኒዎስ |

ማጠቃለያ

ባህል የሀገር ሁለንታዊ መግለጫ በመሆኑ ነባራዊ የሃገራችን የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች ማህበረሰቡ በአለማዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ህይወት በእጅግ ይጠቀሙበታል፡፡ ህብረ ብሄር አንድነታችን ውበታችን በሚለው በጋራ አብሮ መኖር እሴቶቻችን እንጠብቃለን፡፡ እያንዳንዱ ታሪክ ነጋሪ ወይም ደራሲ ታሪኩን ለአንባቢ (ተደራሲ) የሚያቀርበው ህዝቡን ያስደስታል የፈለግሁትን ማህበራዊ ጉዳይ ያሳይልኛል ብሎ በሚመርጠው ዘዴ ነው፡፡ ታሪኩ በየተኛው ዘዴ ይተረክ፤ እንዴትስ መሳጭ በሆነ መልኩ ቀርቦ ሳቢ ይሁን በማለት በተለያዩ ፍሬ ነገሮች በማቀናጀት ያቀርባል፡፡

ተራኪ፡- በታሪክ ፈጣሪው (ደራሲው) እና በተደራሲው መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚተረጉምና የሚገልፅ፤ አልፎ አልፎ በግልፅ አብዛኛውን ጊዜ ግን በታሪኩ ውስጥ ሆኖ በውስጥ አዋቂነት የሚኖር፤ የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚያቀርብልን ነው፡፡

## ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1.የምታቁትን ታሪክ ወይም ተረት ነድፋቹ አሳዩ፡፡

መስሪያ ቁስ

ሀ. በእርሳስ　　ለ. በኢንክ

ሐ. በቀለም　　መ. ወረቀት

## መልመጃ 1

### የሚከተሉትን ጥያቆዎች አዛመዱ

1. ተውኔታዊ የትረካ አንፃር　　ሀ. እኔ እያለ ያቀርባል
2. አንደኛ መደብ የትረካ አንፃር　　ለ. ፍርድና ሳይቀር ይሰጥበታል
3 ደራሲውንና ተደራሲውን ያገናኛል　　ሐ. ዳር ሆኖ ይታዘብበታል
4. ሁሉን አወቅ የትረካ አንፃር　　መ. ሰዓሊ

ሠ. ተራኪ

# ምዕራፍ 4

# ሥነ ውበታዊ ጥቅም (ዋጋ)

## መግቢያ

የሙዚቃ ዕውቀት ሃገራችንን ሁለንተናዊ መልካም ገፅታ ከማሳወቅ ባሻገር ስለ ሰላም የምንዘምርበት፣ ታሪክ የምናውቅበት፣ መልካም አስተሳሰብን የምናፈልቅበት፣ ደስታን የምንጋራበት፣ አለም አቀፍ ቋንቋ የምናውቅበት፡፡ በየዘመናት በትውለዶች መካከል የነበረውን ያለውን እውቀት በማቀራረብ አሸጋጋሪ በመሆኑ ስለሙያው ማድነቅ ውዝዋዜ በአለማዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ህይወት ውስጥ ከሙዚቃ ጋር ቁርኝት ያለውና ማህበረሰብ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ ስሜቱን በመላው የሰውነት ክፍሉን በመንቀሳቀስ ደስታውን የሚገልፅበት ነው፡፡

ሀገር በቀል ክዋኔ ለአንድ ሀገርም ይሁን ማህበረሰብ ሰላም የሚፈጥርበት፣ ታሪክ የሚነግርበት፣ ሃሳብ የሚያፈልቅበት፣ ሙያን የሚለምድበት፣ እውቀት የሚያገኝበትና የሚያስተላልፍበት፣ ደስታውን የሚያጋራበት፣ አብሮ የመኖር መሰረት የሆነ የችግር መፍቻ ቁልፍ ነው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ነገሮች በትውፊት (ልማዳዊ የውርስ ዘዴ) በማስተላለፍ በተለያዩ ዘመናትና ትውልዶች መካከል ያለውን የጊዜና የእውቀት ልዩነት በማቀራረብ ድልድይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

(ዋጋ)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የሙዚቃ እውቀት ጠቀሜታን በሚገባ ትረዳላችሁ
- የተላያዩ ሙዚቃዎችን በማድመጥ የዜማውን ፍሰት ትችላላችሁ

## 4.1.1 የዜማ ክዋኔዎች

ዜማዎች (ሙዚቃዎች) የሚከወኑት ማህበረሰቡ መገልገል ባለባቸው ቦታዎች ቀደም ሲል እንደዛሬው መገናኛ ብዙሃን ከመስፋፋታቸው በፊት መንፈሳዊ ሙዚቃ በቤተ እምነቶች አለማዊ ሙዚቃ በህብረተሰብ በሚሰባሰብበት አካባቢና እንደዚሁም በግለሰቦች መኖሪያ ቤት ይከወን ነበር፡፡ በተለይም በአለማዊው ሙዚቃ ቀደም ሲል የተሰሩና አሁን ድረስ ዘመን ተሻጋሪ በመሆን አሁን ላለው ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃዎች በመገልገል ላይ ያሉት ሀገራዊ ሙዚቃ ቅኝቶች መሰረት የሆኑት ዜማዎች ትዝታ፤ባቲ  ፤አንቺሆዬ

### የክዋኔ እይታዎች

- በህብረተሰቡ የጋራ ተግባራት ላይ የተመሰረተ መሆኑ
- ዜማ በውዝዋዜ መታጀቡ፡፡
- በህብረተሰቡ  መገልገያ  በሆኑት የባህል መሳሪዎች ታግዞ ይቀርባል፡፡

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄወች ዓ/ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የሀገራችን ሙዚቃ በህብረተሰቡ ባህል ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡
2. ዜማዎቻችን ያሬዳዊ ዜማ መሆኑ የስልጣኔ ምልክት አይደለም፡፡
3. ባህላዊ ውዝዋዜ የማንነታችን መገለጫዎች ናቸው፡፡
4. ከበሮ ከትውፊታዊ ቁሳቁሶች አንዱ መሆን ይችላል፡፡

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ባህላዊና ዘመናዊ ውዝዋዜ ታደንቃላችሁ
- ሰሜት ባሳደረባችሁ የውዝዋዜ አይነት በተግባር ትወዛወዛላችሁ

## የውዝዋዜ አይነቶች

የውዝዋዜን ጥበብ ማድነቅና ሀገር በቀል ውዝዋዜዎችን የብሄር ብሄረሰቦችን ባህል ትውፊት ባለበትና በነበረበት ወግና ልማዱ መሰረት የሚከወን አልባሳትን ጨምሮ የሚከወን የባህል ውዝዋዜ ስንለው የውጭውን የውዝዋዜ ስልት ደግሞ ዳንስ በአብዛኛው የተለያዩ ዘመናዊ የእንቅስቃሴ ስልቶችን ያጠቃልላል

ዊ ጥቅም (ዋጋ)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የትውፊታዊ ተውኔትን ምንነት
- የትውፊታዊ ተውኔት ባህርያትን እና
- ክዋኔዎቹን ትረዳላችሁ፡፡

ትውፊታዊ ተውኔት ከማህበረሰቡ ልማዶች፣ እምነቶች፣ ክብረ በዓላትና ስነቃሎች ላይ ተመስርቶ የሚመደረክ ባህላዊ ትርኢት ነው፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት ከስርዓተ አምልኮታዊ ተውኔት የሚለየው አለማዊ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጭምር ትኩረት አድርጎ ስለሚሰራ ነው፡፡ ትኩረቱም በይበልጥ በማህበረሰቡ እውነታዎችና ድርጊቶች ላይ ሲሆን ቁምነገሮችንና ችግሮችን ለማሳየትም ያገለግላል፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት በቡድን የሚከወንና እንዲሁም ተመልካቹ እንደ አስፈላጊነቱ ተሳታፊ የሚሆንበት ሀገር በቀል ጥበብ ነው፡፡

ትውፊታዊ ተውኔት የማህበረሰቡን ማንነት ከማሳየትም ባሻገር ማህበረሰቡ ሲጨንቀው ለጭንቀቱ ማስወገጃና ወኔ ማሰባሰቢያ፣ ተፈጥሮ ስትጨክንበትና ጣጣ ስታመጣበት የችግሩ መቋቋሚያ፣ ሲደሰት የደስታው መግለጫ፣ ለስራ አንድነትንና ህብረትን መፍጠሪያ እንዲሁም ፈጣሪውን ማመስገኛ በማድረግ ይጠቀምበታል፡፡

ለምሳሌ፡- በአደን የሚተዳደር ማህበረሰብ ስለአደን ምንነት፣ የጦር አያያዝ፣ የጥይት (ጠብመንጃ) አተኳኮስ፣ የአውሬ ቅኝት እንቅስቃሴ፣ አውሬው ሲቆጣ እንዴት ማምለጥ እንደሚቻል፣ አውሬውን ከገደሉ በኋላ እንዴት እንደሚከፋፈሉ፤ ማለትም መጀመሪያ የወጋው ሰው ምን እንደሚወስድ፣ ሁለተኛው ምን እንደሚገባው እና ሌላው ተሳታፊ እንዴት እንደሚከፋፈል ... ከማሳየቱም በተጨማሪ የአዳኙን ስም ሰያሜ፣ ክብርና የአለባበስ ሁኔታ በሙሉ በድርጊታዊ ክዋኔ ከወዲያ ወዲህ እየተንቀሳቀሱ፤ በቃላዊ ገለፃ በመታገዝ የደጊቱ ባል የበላይ አባት፣ አንደኛ ወጊ፣ ወንድ አስደግዳጊ... ወዘተ. እያለ ይሸልላል፡፡ ገዳይ የጣለውን አውሬ ይዞ ከማህበረሰቡ ጋር ሲቀላቀል፣ የሚደረግለትን አቀባበል፣ የውደሳና የሙገሳ ዘፈኖች፣ ግጥሞችና ጭፈራዎችም ሊቀርቡለት ይችላሉ፡፡

### 4.3.1. የትውፊታዊ ተውኔት ባህርያትና ክዋኔዎች

ትውፊታዊ ተውኔት የራሱ የሆኑ ባህርያትና የመከወኛ ጊዜዎች አሉት፡፡

- በማህበረሰቡ እውነተኛ ተግባራት ላይ የተመሰረተ በመሆኑና በሌሎች ከማህበረሰቡ ውጪ በሆኑ ሰዎች ሲከወን ተጠንቶ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ከፈጠራ ነፃ ሁኖ የማህበረሰቡን ገፅታ ሳይበርዝ ያሳያል፡፡
- ተመልካቹ የታሪኩ አካል ሆኖ በንቃት ይሳተፋል፡፡
- በዜማና በውዝዋዜ ይታጀባል፡፡
- በማህበረሰቡ መገልገያ ቁሳቁሶች ታግዞ ይቀርባል፡፡
- በክዋኔዎች መካከል የሚቀሩ ሃሳቦችና ለማቅረብ አስቸጋሪ የሆኑ ድርጊቶች በተራኪ አማካኝነት ተዘርዝረው ይቀርባሉ፡፡

የሚቀርቡበትን ጊዜዎች በተመለከተ በዓመት አንድ ጊዜ የሚቀርቡ እንደ እንቁጣጣሽ፣ ገና፣ መውሊድ፣ ቡሄ… ወዘተ. ሲጠቀሱ ወቅትን መሰረት አድርገው የሚከወኑ ደግሞ፡ ሰርግ የፆም ወቅት ከመግባቱ በፊትና ፆም ከተፈታ በኋላ፤ሲከወን ደቦ ስራ በሚበዛበት ጊዜ ይከወናል፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ማንኛውም ጊዜ በትብብር የሚከወኑ በመዋጮ፣ እድር፣ ማህበር የሚታገዙ እንደ ውልደት፣ ሞት፣ እንዲሁም እርቅ የመሳሰሉ የሆነ ክስተትን ተከትለው የሚከወኑ ተግባራትን ያካትታል፡፡

## የመልመጃ ጥያቄወች

I. የሚከተሉትን ጥያቄወች ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ትውፊታዊ ተውኔት የፈጠራ ክዋኔ ነው፡፡
2. በትውፈታዊ ትውኔት ውስጥ ተራኪ ያስፈልጋል፡፡
3. ባህላዊ ዳኝነት ትውፊታዊ ክዋኔ አይደለም፡፡
4. ከበሮ ከትውፊታዊ ቁሳቁሶች አንዱ መሆን ይችላል፡፡

II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት አንዱ የትውፊታዊ ተውኔት ባህርይ አይደለም?
   ሀ. እውነተኛ ተግባር ላይ ይመሰረታል  ለ. በዜማ ይታጀባል፡፡
   ሐ. ውዝዋዜን አይፈልግም  መ. ሁሉም መልስ ናቸው
2. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በአመት አንዴ ይከወናል?
   ሀ. እንቁጣጣሽ  ለ. ቡሄ  ሐ. መውሊድ  መ. ሁሉም
3. ወቀትን መሰረት አድርጎ የሚከበረው የቱ ነው?
   ሀ. ደቦ  ለ. ሰርግ  ሐ. ገና  መ. ሀእና ለ
4. አስፈላጊ በሆኑ ጊዜዎች ክስተትን ተከትሎ የሚከወን ተግባር የቱ ነው?
   ሀ. እርቅ  ለ. እርሻ  ሐ. ሀ እና ለ  መ. መልሱ አልተሰጠም

ጋ)

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

**ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የዕይታ ጥበብን በመረዳት በዚህ ዘርፍ የተሰሩ የማህበረሰቡ ታሪክ ቅርስየፈጠራ ውጤቶችን ትለያላችሁ::
- በአገራችን ብዙ ታዋቂ ስዓሊያን መካከል የሜትር ሎሬት ማዕረግን ያገኙ የመጀመሪያው ታላቅ ሰው ትተዋወቃላችሁ ::
- እጅግ የተከበሩ የአለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌን የስዕል ስራዎች ታደንቃላችሁ ::
- የ21 ክፍለ ዘመን እጅግ ታላቅ አርቲስትና የምርጦች ምርጥ ተብለው መሸለማቸውን ታደንቃላችሁ ::
- የአርቲስቱን የስዕል ጥበብ ውጤቶች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግየተሻለ የማድነቅና የመሆን ፍላጎት ትጨምራላችሁ::



እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ




እናት ኢትዮጵያ1959ዓ.ም

## ቅድመ ንባብ

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ

በኢትዮጵያ ላይ ክፉ አትይ ክፉ አትስማ ክፉት አትናገር ይህ የአርቲስቱ ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ መሪ ቃል ነዉ:: በአለማችን ላይ ምርጦች አሉ ደግሞ የምርጦች ምርጥ አለ እርሱ የ21 ክ/ዘ ታላቅ ሰው ወይም ግሬት ማይንድስ ተጎናፀፈዋል:: የአሜሪካን ባዩግራፊካል ኢንስቲትዩት በጥበብ ስራዎቻቸው ላበረከቱት ድንቅ ስራ የበዛ አድናቆትን ገልፆአ ዋሽግተን ዲሲ በተካሄደው ወርልድ ፎርም ላይም ከአንድ ሺህ እጩዎች መካከል ተመርጠው የ21ኛው ክ/ዘመን የታላቅ አእምሮ ባለቤት ተብለው ተሸለሙ የኢትዮጵያ የአንባሳዳር ማህረግም አገኝተዋል እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ናቸው:: ሀገራችን ካፈራቻቸው ታላላቅ የስነ ጥበብ ሰዎች መካከል በዘመናዊ የ ዕይታ ጥበብ ቀዳሚ ናቸው::ትምህርታቸውን የተከታተሉት እንግሊዝ ሀገር ሲሆን የመጀመሪያ ፍላጐታቸው ኢንጂነር መሆን ነበር ከፍላጎታቸው በኂላም በዕይታ ጥበብ በቀለም ቅብ፣ በኪነ-ቅርፅ ኪነ-ህንፃና የመስታወት ስዕል አስራር አጠኑ:: ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኂላም ሆነ ታላላቅ ሽልማቶችን ከተቀበሉ በኂላ ሀገራቸው ተመልሰው የስዕል ስራቸውን ይጀምራሉ::

በመኖሪያ ቤታቸው አልፋ ቪላ በሚባለው ውስጥ እንግዶቻቸውን ያስተናግዳሉ:: አርቲስቱ የተወለዱት 1932 ዓ.ም አንኮበር ከተማ ነው:: የሀገራችን ታላቁ ደራሲ ባህሉ ግርማ ኢሊባቡርን መልከአ ተፈጥሮ ውበት ወንዙን፣ ኮረብታውንና ደኑን ሲገልፅ በአፈወርቅ ተክሌ ጣቶች የተሰሩ ስዕሎች ይመስሉ ነበር ያለው::



ሥዕል፡-በመኖሪያ ቤታቸው አልፋ ቪላ በስራ ላይ

አዘውትረው ለኢትዮጵያ ምን ስራህላት ብላ ትጠይቀኛለች ይላሉ:: የጣታቸው ሰራዎችም በአለም ከታወቁት እናት ኢትዮጵያ፣ የሰሜን ተራሮች፣ የመስቀል አበባና ሌሎች በርካቶች ይሄን የሚያሳዩ ናቸው:: ሽልማት የስራ ውጤት ነው አደል የሚባለው ከወጪ ሀገር ካገኙት ሽልማቶች ውጪ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸለሙት ከንጉሱ ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ እጅ ነው:: ከአፍሪካ ካገኟቸው ሽልማቶች ውስጥም ጋና፣ ናይጄሪያ፣ ግብፅ ፣ ሴኔጋል ሲሆኑ የአሁኑን ሽልማት ጨምሮ ከ97 በላይ ሽልማቶች አግኝተዋል:: ኢትዮጵያ በተለያዩ ኢትዮጵያን በተለያዩ ጊዜያት ስሟን የሚያስጠሩ ባንዲራዋን በአለም አደባባይ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረጉ ጀግኖች ልጆች አሏት ከነዚህም ውስጥ እጅግ የተከበሩ የአለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የታላላቆቹ ታላቅ የሀገራት መሪዎች የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ሳይንቲስቶች ፣ ደራሲያን፣ ሳአሊያን ተመርጠው የሀገራቸውን ባንዲራ ሰማቸውንና የሕይወት ታሪካቸውን ተፅፎ ወደ ጨረቃ ሲላክ የአርቲስቱ ሕይወት ታሪክ ተፅፎ ከኢትዮጵያ ባንዲራ ጋር ጨረቃ ከተቀበረው ግልባጭ የሁላችንም ክብር ሆኖ ይገኛል :: አርቲስቱ የአራት አካዳሚዎች አባል በመሆናቸው ስራዎቻቸው በታላላቅ ታሪኮች በታላላቅ ሙዚሞች በቋሚነት ለሕዝብ ክፍት ሆነው ስለሚገኙ በየደረጃው ሜትር አርቲስት ወይም የስነ ጥበብ ሊቀ የአለም ሎሬት እጅግ የተከበሩ የሚባሉ ማህረጎችን አስጥቶአቸዋል ::ስለ አርቲስቱ በተለያዩ ቋንቋዎች መፅሐፍ ተፅፎላቸዋል :: በሚሸለሙበትና የሚጋበዙበት መድረክ ላይ ስለ ሰው ዘር መገኛነታችን፣ ሰለ ኪነ ሕንፃዎቻችን፣ስለነፃነታችን፣ስለ ባህልና ወጋችን ይስብካሉ::አንደበታቸው በቃላት ጣቶቻቸው በቀለምና ብሩሻቸው ያውራሉ ስለ ሀገራቸው ተናግረው አይጨርሱም::



ሥዕል፡-የአርቲስቱ የመስታወት ሥዕል በሙዚዩም ውስጥ

ከዮናይትድ ስቴት አሜሪካ የአሜሪካ ባየግፊካል ኢንስቲትዩት እና የዩናይትድ ኪንግደም ኢንተርናሽናል የባየግራፊካል ሴንተር የ21 ክፍለ ዘመን እጅግ ታላቅ አርቲስትና የምርጦች ምርጥ በመባል በተለያዩ መድረኮች ላይ ለዘመናት ለአለም ላበረከቷቸው የስነ ጥበብ ስራዎችቸውና በዋሽግተን ዲሲ እ አ ከሰኔ 29 - ሐምሌ 4 ቀን 2009 ዓ.ም ባዘጋጃው ኢንተርናሽናል ኢግዚብሽን ላይ ኢትዮጵያንና አፍሪካን የሚወክሉ ሦስት አዳዲስ የስነ ጥበብ ስራዎችን አቅርበዋል::

እነዚህም ስዕሎችም የኢትዮጵያን፣ የአፍሪካንና የአለምን የስነ ስዕል ያሳደጉ ሆነው በመገኘታቸው ኢንተርናሽናል ባዮግራፊካል ሴንተር የአሜሪካ ባዮግራፊካል አንንስፒቲዎት ባዮግራፊካል ኢንስቲዩትዎት የእድሜ ልክ ክብር ወይም ታላቅ ሰው ብሎ ሽልማት ታላቅ ሰው ብሎ ሽልማት አበርክቶላቸዋል::




ሥዕል፡-የእድሜ ልክ ክቡር ወይም ታላቅ ሰው ሽልማት እ አ
ከሰኔ 29 - ሐምሌ 4 ቀን 2009 ዓ.ም

## ማጠቃለያ

ሀገር በቀል እውቀቶችን በሙዚቃ በተለያየ ስልት ማስተዋወቅ ማንነትን ከማስተዋወቅ አልፎ የራስ አሻራን አጉልቶ ማውጣት ነው፡፡

ሀገር በቀል ውዝዋዜዎቻችን ኩራታችን ቱባ ባህላችንን ማስተዋወቅ አሻራችንን ከማጉላት ባሻገር የማንነታችን መግለጫም ጭምር ነው፡፡

ትውፊታዊ ተውኔት ከማህበረሰቡ ልማዶች፣ እምነቶች፣ ክብረ በዓላትና ስነቃሎች ላይ ተመስርቶ የሚመደረክ ባህላዊ ትርኢት ነው፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት ከስርዓተ አምልኮታዊ ተውኔት የሚለየው አለማዊ በሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ጭምር ትኩረት አድርጎ ስለሚሰራ ነው፡፡ ትኩረቱም በይበልጥ በማህበረሰቡ እውነታዎችና ድርጊቶች ላይ ሲሆን ቁምነገሮችንና ችግሮችን ለማሳየትም ያገለግላል፡፡

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የሀገር በቀል ዕውቀቶች በክወናና በዕይታ ጥበባት ማድነቅ ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም አዳምጦ መረዳት፣ የተለያዩ ታዋቂ ዕይታ ጥበባት ስዎችንና ስራዎቻቸውን ማየት ናቸው፡፡

- አርቲስቱ የተወለዱት1932ዓ.ም አንኮበር ከተማ ነው፡፡ የሀገራችን ታላቁ ደራሲ ባህሉ ግርማ የኢሊባቡርን መልከአ ምድር የተፈጥሮ ውበት ወንዙን፣ኮረብታውንና ደኑን ሲገልፅ በአፈወርቅ ተክሌ ጣቶች የተሰሩ ስዕሎች ይመስሉ ነበር ያለው፡፡
- የአሜሪካን ባዬግራፊካል ኢንስቲትዩት በጥበብ ስራዎቻቸው ላበረከቱትድንቅስራ የበዛ አድናቆትን ገልፆአ ዋሽግተን ዲሲ በተካሄደው ወርልድ ፎርም ላይም ከአንድ ሺህ እጩዎች መካከል ተመርጠው የ21ኛው ክ/ዘ የታላቅአእምሮ ባለቤት ተብለው ተሸለሙ የኢትዮጵያ አንባሳደር ማህረግም አገኙተዋል እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ላይ ክፉ አትይ ክፉ አትስማ ክፋት አትናገር ይህ የአርቲስቱ ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ መሪ ቃል ነዉ፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ከአፍሪካ ሀገሮች ካገኟቸው ሽልማቶች ውስጥም ጋና፣ ናይጄሪያ፣ግብፅ፣ሴኔጋል ፡፡

ለ. የአርቲስቱ ሕይወት ታሪክ ተፅፎ ከኢትዮጵያ ባንዲራ ጋር ጨረቃ ተልካል፡፡

ሐ. አርቲስቱ የአራት አካዳሚዎች አባል በመሆናቸው ስራዎቻቸው በታላላቅ ታሪኮች በታላላቅ ሙዚሞች በቋሚነት ለሕዝብ ክፍት ነው፡፡

መ. ስለ አርቲስቱ በተለያዩ ቋንቋዎች መፅሐፍ ተፅፎላቸዋል ፡፡

II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በታሪኩ መሰረት በቃላችሁ መልሱ::

ሀ. አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የተወለዱት መቼ ነው?

ለ. አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ትምህርታቸውን የተከታተሉትየት ነው?

ሐ. አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የመጀመሪያ ፍላጐታቸው ምንድነው?

መ.አዘውትረው ኢትዮጵያ ------------ ብላ ትጠይቀኛለች ይላሉ::

ሠ. በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸለሙት በማነው?

III. ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ::

1. የሀገራችን ታላቁ ደራሲባህሉ ግርማ የኢሊባቡርን መልከአ ምድር ተፈጥሮ ውበት ወንዙን ፣ ኮረብታውንና ደኑን ሲገልፅ ------------ ጣቶች የተሰሩ ስዕሎች ይመስላሉ ነበር ያለው::
2. ሀ- ሠአሊ መዝገቡ ተሰማ ለ-ሠአሊ አፈወርቅተክሌ ሐ- ሠአሊ ለማ ጉያ
3. አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በሙሉ የክብር ስም ሲጠሩ እንዴት ነው?
4. እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ------------ ሀገር አንባሳደር ናቸው::

ሀ-የኢትዮጵያ ለ-የእንግሊዝ ሐ-የአሜሪካ መ-የጀርመን

# ምዕራፍ 5

## ጥመርታ፣ዝምድናና ትግበራ

### የክወናና የዕይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኂላ፡-

- የአካባቢን ንፅኅና ስለ መጠበቅ ትረዳላችሁ
- የብክለት ምንነትና አይነቶችን ታውቃላችሁ
- ሙዚቃ የትምህርት አጋዥነት በሚገባ ታውቃላችሁ

### 5.1.1 አካባቢ ብክለት

- የአየር ብክለት የሚከሰተው ስራ ቦታዎችን በማሞቅ ለምሳሌ በተሽከርካሪዎች በሚለቀቁ ጋዞች ከፋብሪካ በሚለቀቁ አላስፈላጊ ንጥረ ነገሮች
- የአፈር ብክለት የሚከሰተው እንደ ፌስታል የአፈሩን ለምነት ከሚከለክሉ ነገሮች
- የውሃ ብክለት አላስፈላጊ ቆሻሻዎች በውሃ መውረጃ በዮች ላይ መጣል
- የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ ብክለት ሰዎች በሚተላለፉበት መንገዶች የውሃ መውረጃ በዮች ዲሾች ላይ ሲወገዱ፤ የድምፅ ብክለት በመኖሪያና በስራ ቦታዎች አላስፈላጊ የጎላ ድምፅ መልቀቅ
- የምስል ብክለቶች ህግና ደንብን ባልተከተለ መልኩ ማስታወቂያ ኖቶችን በመብራት ፖሎች በግድግዳ በተሽከርካሪ መለጠፍ ናቸው፡፡

## 5.1.2 የአካባቢ እንክብካቤ

በኬሚካል ውህደቶች፣ በባዮሎጂካል ሂደቶች እንዲሁም በሙቀት ለውጥ አማካኝነት የሚፈጠሩ ቆሻሻዎችን የማጥራትና የማስወገድ፣ አየርንና ውሃን የማጣራት፣እንዲሁም በአደጋ ወይም በቆሻሻ ክምችት የተበከለን የመሬት አካል ወደ ተፈጥሮኣአዊ ይዘቱ የመመለስ ስራዎች መስራት ተፈጥሮን መመለስ ማለት ነው።
ከዚህ በላይ በዝርዝር በቀረቡት ላይ ሁላችንም በአካባቢያችን ጥንቃቄ ብናደርግ በተፈቀደላቸው ቦታዎች ላይ ብቻ የሚያስፈልገውን ክዋኔ ብናደርግ ለፅዳት የሚወጣው ወጪ ከመቀነስ አልፎ ለሀገራችን እድገት ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል

**መልመጃ**

ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት የሆነውን ሐሰት በማለት መልስ ስጡ

1. ቆሻሻ በአግባቡ ከተጠቀምንበት ሃብት ይሆናል ።
2. የድምፅ ብክለት በዋነኝነት የሚያጠቃው የጆሮ ክፍልን ነው።
3. ቆሻሻን በቦታው መጣል የስልጣኔ ምልክት ነው ልንል አንችልም።

### የትምህርቱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ

- ከሰው ልጅ የእለተ ከእለት የህይወት እንቅስቃሴ ጋር ዝምድና ስላለው ነባራዊ ሁኔታን ራስን ከትራፊክ አዳጋ መጠበቅ በዘመኑ በተከሰተው ኮቪድ ራስን ከንክኪና ህመሙ ሊተላለፍ ከሚችልባቸው ነገሮች ሁሉ መጠበቅ ከኤች አይቪ በሽታ ራስን ስለመከላከል፤ ፆታዊ ትንኮሳን በመሳሰሉትና ለጤና ጎጅ፤ ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ መቆጠብን በሚገባ መረዳት።
- የሙዚቃ አለማቀፋዊነትን በሚገባ ማወቅ።
- የትምህርት የመማር መማስተማርን ሂደት በተሳለጠ መልኩ እንዲካሄድ አጋዥነቱ የጎላ ነው።

## 5.2.1 የሙዚቃ ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር

✪ ለሂሳብ፡- ተማሪዎች በቀላሉ አራቱን የሂሳብ መደቦች መደመር፣ መቀነስ ማካፈልንና ማባዛትን እንዲረዱ ያስችላል መረዳት።
✪ ለውጭ ቋንቋዎች፡- እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ አረብኛ ወዘተ በመዝሙር አማካኝነት መረዳት።
✪ ለሰውነት ማጎልመሻ /አካልብቃት/ እንቅስቃሴ የሰውነት ክፍልን ለማንቀሳቀስ ሴሎችን ለማነቃቃት የሙዚቃ ስልተም እጅግ ጠቀሜታ አለው።
✪ ለታሪክ ትምህርቶች፡- ሃላፊውን ለመዘከር ነባራዊውን ለማጎልበት ትልቅ ሓይል ሰጪ አጋዥ በመሆን ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱበት የሚችሉበት ነው።

ለሙዚቃ ትምህርት የዘርፉ ምሁራን የማስተማሪያ ሞጅሎች ተጠቅመውበታል እነዚህም አሁን ለምንጠቀምበት የማስተማር ስነ ዘዴ ለሙያው መሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። ከነዚህም በከፊል

**የዳልክሮዝ** ሞዴል ስልተ ምት(ሪትሚክ) ኖታ ንባብ (ሶልፌጅ) በዚህ መነሻነት መስማት ችሎታን ለማዳበር ሙዚቃ አዕምሮና አካል በማዋሃድ ዋነው ቁልፍ ነው።

**ዞልታን ኮዳሊ** የሶልፋ ዘዴ የማድመጥ ሰልጠና ያለሙዚቃ መሳሪያ ሙዚቃን ማንበብ የእጅ ምልክቶች ተማሪዎች በሚዘምሩበት ጊዜ ድምፆችን ለማሰታወስ የሚረዱ ምልክቶችን ደርሰዋል።

**ካርል ወፍ** ፡- ሙዚቃ ትምህርት የሚጀምረው ከእንቅስቃሴ ላይ ነው ይህንንም ዘዴ ሲገለጽ
✪ ምት ሕይወት ባለው በማንኛውም ውስጥ አለ
✪ ንግግር እንቅስቃሴና ሙዚቃ ተሳስረው ይገኛሉ
✪ የንግግር ለዛ በምትና በድምፅ ላይ ነው

**ሲኒቺ ሱዙኪ** በሙዚቃ ሁሉም ህፃናት የተማሩ ይሆናሉ

### 5.2.1.1 ሙዚቃ ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች የሚሰጣቸው ጥቅሞች

✪ የመጨነቅ ሁኔታን ለመቀነሰ አዕምሮን በማዝናናት የማስተማር ሚና ይጫወታል።
✪ በሰውነታችን ውስጥ በቀጥታ የምግብ መዋሐድ ፍጥነት ልብ አመታትን በማስተካከል ባሻገር ሆርሞን እንዲመነጭ በማድረግ የትምህርት ክትትልና የማዳመጥ ችሎታችንን ያዳብራል።

- ✪ በትምህርታቸው ደከም ያሉ ተማሪዎች አዕምሮ በማነቃቃት የማስታወስ ችሎታን ያጎለብታል፡፡
- ✪ ከሂሳብ ስሌት እኩል ሀሳብን ለመሰብሰብ አንድን ነገር በቀላሉ እንድንረዳ ያደርጋል፡፡
- ✪ ሰሜትን በመቀስቀስ ደረጃ የረጅም ጊዜ ማስታወስ ችሎታ ያዳብራል፡፡
- ✪ የተማሪዎች ከደረጃ ወደ ደረጃ የመለወጥ ክህሎትን ያዳብራል ያፋጥናል፡፡
- ✪ አለም አቀፍ ቋንቋ ነው፡ ሐይል ያለውና ለሌሎች ትምህርቶች መልህቅ ነው፡፡

መልመጃ

ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ

1. ሙዚቃ አለም አቀፍ ቋንቋ እነዲሆን ያስቻሉት ሁለገብ መሆን መቻሉ ነው፡፡
2. ስሜትን ይሰጣል ስንል በተገደበ መልኩ ብቻ ነው፡፡
3. ሃይል ያለው መልህቅ ስንል ለትምህርቶች ማቆሚያ መሰረትማለታችን ነው፡፡
4. ማንኛውም እንቅስቃሴ ስልተ ምት ነው፡፡

## 5.2.2 ውዝዋዜን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማጣመር

ሙያው በሁሉም ዘርፎችን መድረክ ገላጭ መሆኑን ማሳወቅ ነው፡፡

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ➲ ውዝዋዜ ሁሉንም ዘርፍ በመድረክ የአካል እንቅስቃሴ ገላጭ መሆኑን ታውቃላችሁ፡፡

ጥምር ገላጭነት

ውዝዋዜ የጥበብ፤ የሳይንስ፤ የህብረተሰብ ወዘተ በአጠቃላይ ለሰው ልጅ የማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ እድገቶች አዲስ ለሚፈጠሩትም ሆነ ለነባራዊው እውቀቶች ቀጣይነት በመድረክ እንቅስቃሴ ገላጭ ነው፡፡

## 5.2.3. ተግባራዊ ክዋኔን ማሳየት

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ታሪኩን ታነባላችሁ
- የተረዳችሁትን ታብራራላችሁ
- የገፀ- ባህርያትን ማንነት ትገልፃላችሁ
- ታሪኩን አስፋፍታችሁ ትፅፋላችሁ
- ቃለ-ተውኔቱን በአእምሯችሁ በመያዝ መድረክ ላይ ታቀርባላችሁ

### ነቃይና ተካይ

#### ትዕይንት1

በዚህ አጭር ተውኔት ውስጥ የተለያዩ አላማዎችን የያዙ ገፀ- ባህርያት ተካተውበታል፡፡

ሀርሚና፡ አገር ወዳድና ምስጉን የልማት ሰው

ተንኮሉ፡ ተንኮለኛና ስልጣን ፈላጊ የሀርሚና የስራ ባልደረባ

እውነቱ፡ የተንኮሉና የሀርሚና የስራ ባለደረባ ሲሆን ለእውነት የቆመ ሰው ነው፡፡

አባጃዱ፡ የዝንም አካባቢ የሃይማኖት መሪ

ምዕመናን፡ የዝንም ነዋሪዎች

ዳኛ፡ የዝንም አካባቢ ፍርድቤት ዳኛ

ቦታው ኢትዮጵያ ዝንም የሚባል አካባቢ ሲሆን ዘመኑ አሁን ያለንበት ነው፡፡

ሀርሚና በክረምት ዝናቡ ሳይቆምና ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው ሳይመለሱ በጎ ፈቃደኞችን በመያዝ በየአካባቢው እየተዘዋወረች ችግኝ ትተክላለች፡፡ ዛሬ ቀኑ ሶስት እለቱ ደግሞ ሰኞ ነው፡፡ ሀርሚና ተረኛ በሆነው የዝንም አካባቢ ችግኝ አስተክላ ጨርሳለች፡፡ ተንኮሉ ከሀርሚና ተደብቆ ወደ ዝንም አካባቢ ቤተእምነት በመሄድ ከአንድ አባት ጋር ቆሞ ሲያወራ ይታያል፡፡

ተንኮሉ፡ እንደምን አሉ አባቴ፡፡

አባጃዱ፡ ፈጣሪ ጃዱ ይመስገን ልጄ ማን ነህ አይኔ ደክሞ ሰው መለየት እያቃተ ነው፡፡

ተንኮሉ፡ አይ አባቴ እኔን እንኳን አያውቁኝም፡፡ የተከሰተውን ጉድ አይቼ እንዴት ዝም አሉ ብዬ ለመጠየቅ መጥቼ እንጅ፡፡

አባጃዱ፡ የምን ጉድ ልጄ?

ተንኮሉ፡ እውነት ዛሬ የተፈጠረውን ቢሰሙ ዝም አይሉም ነበር፡፡

አባጃዱ፡ አዎ አልሰማሁም ግን ምን ቢፈጠር ነው እንዲህ ያሳሰበህ?

ተንኮሉ፡ አካባቢያችንን ለችግር ቀያችንን ለመከራ የሚዳርግ ነገር ተደረገኮ፡፡

አባጃዱ፡ ኧረ በስመጃድ በል ልጄ! የምን መከራ ነው የምትለኝ?

ተንኮሉ፡ ሃይማኖታችንን የሚያጠለሽ ምድራችንን የሚያረክስ ተግባር ተፈፀመ ነው የምለው አባ፡፡

አባጃዱ፡ ለምን ግራ ታጋባኛለህ ምን እንደሆነ ለምን አትነግረኝም?

ተንኮሉ፡ ሀርሚና የምትባል ተንኮለኛ ሰው ዛሬ በቀያችን በዓለ አጅኖንን ጠብቃ ችግኝ አስተከለች፡፡

አባጃዱ፡ ምን አልሽኝ?

ተንኮሉ፡ ይኸውልዎ አውቃ በበዓል ጠብቃ በሃይማኖታችን ዘመተች! ችግኝ አስተክላለች፣ አውቃታለሁ ለሃይማኖታችን ጥላቻ አለባት፡፡

አባጃዱ፡ አሀ! እንዲያ ነው ነገሩ?

ተንኮሉ፡ አባ ለአካባቢው እኔ ነበርሁ የተመደብሁት፡፡ ነገ እንጅ ዛሬ አይሆንም ስላት በተንኮል ተነሳስታ ዛሬ አስተከለች፡፡

አባጃዱ፡ ይህ ለክፋት የመጣ መንፈስ አካባቢያችንን ሳይመርዘው ለምዕመኑ ነገውኑ አሳውቃለሁ፡፡

ተንኮሉ፡ አዎ አባቴ እከሌ ነገረኝ ግን አይበሉ እኔ አብሬያት ስለምሰራ እና ስለምከታተላት ተስራዬ ታስባርረኛለች፡፡

አባጃዱ፡ እኔ ባልናገርስ ተግባሯ ይናገር የለ፡፡ ይልቅ ምዕመኑ እንዲመጣ ዙረህ ወረቀት ለጥፍልኝ፡፡

ተንኮሉ፡ እሽ! አባ የተተከለው ችግኝ የማይጠቅምና ወንዝ የሚያደርቅ ነው እኔ በደንብ አውቀዋለሁ፡፡

## ትዕይንት 2

በማግስቱ ጠዋት ምዕመኑ በቤተእምነቱ ተሰብስበው ይታያሉ፡፡

አባጃዱ፡ እንዴት በእለተ አጅኖን ችግኝ ሲተከል ዝም ትላላችሁ ምዕመናን? በሃይማኖት ጠል እና በመሰሪ ሰው የማይጠቅም እና ወንዝ የሚያደርቅ ዛፍ ሆኖ ፍሬ የማይሰጥ መሆኑም ተደርሶበታል፡፡

ምዕመናን፡ ጉርምርምታ

አባጃዱ፡ ዝም በሉ! ይህ ቤተጃዲያንን አፍርሱ ከማለት አይተናነስም! አካባቢው ለከፋ ችግር ከመጋለጡ በፊት አሁኑኑ ሄዳችሁ ንቀሉት፡፡ ይህን ያላደረገ ሃይማኖቱን እንደ ካደ ቆጥሬ በጃዱ ስም እገዝተዋለሁ፡፡

ምዕመናን፡ (በሙሉ ሄደው የተተከለውን ችግኝ ይነቅሉታል)፡፡

## ትዕይንት 3

ተንኮሉና እውነቱ ቢሮ ውስጥ ቁጭ ብለው እያወሩ ይታያሉ፡፡

እውነቱ፡ ሀርሚና ዛሬ ደግሞ ወዴት አካባቢ ነው የምታስተክለው?

ተንኮሉ፡ ተዋት ባክህ እሷ ከዚህ በኋላ አብቅቶላታል፡፡

እውነቱ፡ ምን ማለት ነው እሱ ደግሞ?

ተንኮሉ፡ እንዳቃጠለችኝ ሰራሁላት፡፡

እውነቱ፡ ምን አረግሃት (እውነቱ ቀስ ብሎ ስልኩን ሪከርድ ላይ ያደርገዋል)፡፡

ተንኮሉ፡ ትላንት ወደ አስተከለችበት አካባቢ ሄጄ ነበር፡፡

እውነቱ፡ እሽ!

ተንኮሉ፡ ሃይማኖት ልታረክስ አገር ልታጠፋ እንዳስተከለችው ለሃይማኖቱ አባት ነገርኳቸው፡፡

እውነቱ፡ ምን ብለህ?

ተንኮሉ፡ አውቃ በእለተ አጅኖን እንዳስተከለች እና ችግኙም የማይጠቅም መሆኑን ነገርኳቸው፡፡

እውነቱ፡ እንዴ ግንኮ እሷ ጃዱያን ናት፡፡

ተንኮሉ፡ ምን ለውጥ አለው እሱ ዋናው ስሟ ሀርሚና መሆኑ ነው፡፡

እውነቱ፡ አንተ ግን ትገርማለህ! ይህ ሁሉ ተንኮል ለምን ከስራ ቀረህ ብላ የሶስት ቀን ደሞዝህን ስላስቆረጠችብህ ነው?

ተንኮሉ፡ እሱ ብቻ ሳይሆን እኔ በአገልግሎት እየበለጥኳት ከኋዬ መጥታ ሃላፊ በመሆኗ ጭምር እንጅ፡፡

እውነቱ፡ እሱን አንተም ታውቀዋለህ የትምህርት ዝግጅትህኮ ከሷ ጋር አይገናኝም፡፡

ተንኮሉ፡ ምንም ይሁን ምን ልታከብረኝ ይገባታል፡፡ ደሞ ሴት አትመራኝም፡፡

እውነቱ፡ እና ምን አሰብህ? ምን የሚያረጓት ይመስልሀል?

ተንኮሉ፡ ዛሬ ደውዬ ነበር በሙሉ ነቅለውባታል፡፡ መነቀሉን ሰምታ ስትሄድ ደግሞ እሷንም ቀጠቀጧት፡፡ ከዛ እሷም ክስ መሰረተች እልሃለሁ፡፡

እውነቱ፡ (አዝኖ ራሱን እየነቀነቀ) እና መቼ ነው ቀጠሮው?

ተንኮሉ፡ ነገ ነው ተብሏል፡፡

እውነቱ፡ አንተስ ትገኛለህ?

ተንኮሉ፡ በደንብ ነዋ! ውድቀቷን እስከማይ ቸኩያለሁ፡፡

እውነቱ፡ በል አንተ እህ ካሉህ ብዙ ትናገራለህ፤ ወደ ቤት እንሂድ ሰዓት ደርሷል፡፡

ተንኮሉ፡ አንተስ አትገኝም ጓደኛዬ?

እውነቱ፡ ፍርዱን ለመስማትማ እገኛለሁ፡፡

## ትዕይንት 4

ቦታው የዝጓም አካባቢ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የእለቱ ከሳሽና ተከሳሾች እንዲሁም የእለቱ ዳኛ በቦታቸው ተሰይመዋል፡፡

ዳኛ፡ እሽ ፍርድቤቱ የእለቱን ስራ ይጀምራል፡፡ ተከሳሾች?

ምዕመናን፡ አለን፡፡

ዳኛ፡ ከሳሽ?

ሀርሚና፡ አለሁ፡፡

ዳኛ፡ እሽ ክሱን እንደሚከተለው አነባለሁ፡፡ ከሳሽ ሀርሚና ጌታሁን እንደ ገለፁት በቀን 03/ 11/13 ዓ.ም የተተከሉ ችግኞችን ነቅለውብኛል፡፡ ለምን ነቀላችሁት ብዬ ስጠይቃቸው ደግሞ ደበደቡኝ፡፡ ስለሆነም ይህንን መከራ ለምን እንዳደረሱብኝ ለማወቅና ካጠፋሁ ልክስ ከተበደልሁ ደግሞ ልካስ ይገባል ሲሉ አቅርበዋል፡፡

ምዕመናን፡ አስመሳይ፣ ሌባ፣ ውሸታም (ያጉረመርማሉ)፡፡

ዳኛ፡ ስነስርዓት

(አዳራሹ ፀጥ ይላል)

ዳኛ፡ እሽ ከሳሽ ይህ ሲደረግ ያዩ ወይም የነበሩ ምስክር አሉዎት?

ሀርሚና፡ ማንም የለም፣ ሹፌሬ ነበረ በደረሰበት ከባድ ድብደባ ሆስፒታል ተኝቷል፡፡

ዳኛ፡ እሽ ተከሳሾች ለምን እንደ ነቀላችሁትና ድብደባ እንደፈፀማችሁ የሚያስረዳኝ አለ?

አባጃዱ፡ እኔ አለሁ ክቡርነትዎ ይህች ሴት የኛ ሃይማኖት በማይፈቅደው በአጅኖን እለት አካባቢችን ላይ ችግር የሚያመጣ እና ወንዝ የሚያደርቅ ችግኝ በማስተከሏ ነው ምዕመኑ የተቆጣው፡፡

ዳኛ፡ እርስዎ ወንዝ ሚያደርቅ መሆኑን እንዴት አወቁ?

አባጃዱ፡ እ… እንዴት ነበር ያወቅሁት… አዎ አንድ ምእመን ነግሮኝ ነው፡፡

ዳኛ፡ ያ ሰው ማን ይባላል?

አባጃዱ፡ አይ አትናገር ብሎኝ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ፊቱን እንጅ ስሙን አላውቀውም፡፡

ዳኛ፡ አባት ባልተረጋገጠ ነገር የሰውን መብት መጣስ ትክክል አይደለም፡፡ በህግም ያስጠይቅዎታል፡፡

አባጃዱ፡ የስራ ባለደረባዋ ነኝ ነው ያለኝ፡፡ የሃይመኖታችን ጠላት ናት ቢለኝኮ ጊዜ ነው ሳይቃጠል በቅጠል ብዬ ነው ክቡር ዳኛ፡፡

ሀርሚና፡ ክቡር ዳኛ እኔ ሲጀመር ጃዱያን ነኝ፤ የተተከለውን ችግኝ በሚመለከት ደግሞ ጠቃሚ የሆነና ለአየር ንብረቱ የሚመጥን ሀገር በቀል ችግኝ ነው፡፡ የበዓል ቀን የሚለው እኔም የሀይማኖቱ ተከታይ እንደ መሆኔ ከቆጠርነው ሁሉም ቀን በዓል ነው ታዲያ መች ነው ስራ ሰርተን ለውጥ የምናመጣው?

አባጃዱ፡ ለመሆኑ ግን ጃዱያን ነሽ?

ሀርሚና፡ አዎ አባቴ እኔ ጃዱያን ነኝ ስሜ ከሆነ ችግሩ የልደት ማስረጃ ማምጣት እችላለሁ፡፡

**ዳኛ:** ሀይማኖትሽ ምንም ሆነ ምን ሀገር የጋራ ናት የሚጠቅም ስራ እስከሰራሽ ድረስ መመስገን እንጅ መደብደብ የለብሽም አሁን ፍርድ ቤቱ የተቸገረው ይህን ያረገውን ሰው ማስረጃ አለማግኘቱ ነው፡፡

**እውነቱ:** (ከመቀመጫው ተነስቶ) እኔ ማስረጃ አለኝ ዳኛ፡፡

**ተንኮሉ:** አንተ ምን እያደረግህ ነው? ኧረ አርፈህ ቁጭ በል፡፡

**እውነቱ:** (የሞባይሉን ቅጅ ለዳኛው ያሰማል) ያ ሰው ደግሞ ይህ ካጠገቤ የተቀመጠው ነው፡፡

**አባጃዱ:** (አዝነው አንገታቸውን እየነቀነቁ) ምዕመኑን ማንሆነ መንገድ የመራሁትና ችግር ውስጥ የከተትሁት እኔ ነኝ ይቅርታ አድርጉልኝ ባለማወቅ ሰይጣን ተንኮሉ በተባለ ሰው ላይ አድሮ ቢያሳስተኝ ነውና፡፡

**ዳኛ:** የድምፅ ቅጅው ያንተ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የምትቃወምበት ወይም ወንጀልህን የምታቀልበት ጉዳይ አለህ?

**ተንኮሉ:** የተከበሩ ዳኛ ምንም የምከላከልበት ማስረጃ የለኝም፡፡ ያጠፋሁት ሚስጥሩ ካፌ የወጣ ቀን ነው፡፡ ሌላው የቤተስብ አስተዳዳሪመሆኔና ካሁን በፊት ምንም የወንጀል ሪከርድ የሌለብኝ መሆኑ ከግምት ውስጥ ይግባልኝ፡፡

**ዳኛ:** እሽ ከሳሽ ወደ ፍርድ ከመግባታችን በፊት የሚሉት ነገር አለ?

**ሀርሚና:** እኔ ከኒህ አባትና ከህዝቡ ጋር ምንም ቅራኔ የለብኝም፡፡ ባይሆን በስሜት ከመነዳትና ባልተረጋገጠ ነገር ለርምጃ ከመቸኮል ነገርን ማጣራትና አገርን ማስቀደም ቢለማመዱ ጥሩ ነው፡፡

**ዳኛ:** እሽ ፍርድቤቱ ውሳኔ ያሰማል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ላይ በተገለፀው መሰረት አቶ ተንኮሉ ሆነ ብለው በተንኮል ተነሳስተው ህዝቡን በማሳሳትና የሰው ስም በመጥፋት፣ አልፎ ተርፎም አገርና ወገን ላይ ችግር ሊያመጣ የሚችል ተግባር በመፈፀሙ ህጉ አስራ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ የሚያስቀጣ ቢሆንም ካሁን በፊት የጥፋት መዝገብ የሌለባቸው በመሆኑና የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው በቀን ሰላሳ ችግኝ እየተከሉ ለአምስት ዓመታት እንዲታሰሩ ሲበይን፤ የዝንም ወረዳ ነዋሪዎች ደግሞ ተበዳይን ይቅርታ በመጠየቅ ለሶስት ተከታታይ ቀናት በቀን አምስት ሺ ችግኝ እንዲተክሉ በማለት በይኗል፡፡ የዛሬ ችሎት በዚህ ያበቃል መዝገቡ ወደ ፍርድ ቤት ይመለስ፡፡

## መልመጃ 1

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነትን እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ሀርሚና የእስልምና እምነት ተከታይ ናት፡፡
2. እውነቱ ሃቀኛና አርቆ አሳቢ ነው፡፡
3. አገር የግል፤ ሃይማኖት የጋራ ሀብት ነው፡፡
4. ተንኮሉ ጥቅምና ወንበር ፈላጊ ነው፡፡
5. የተተከለው ቸግኝ የማይጠቅምና ወንዝን የሚያደርቅ ነው፡፡
6. ዳኛው ፍርደ ገምድልነት ይታይባቸዋል፡፡

## 5.2.4. የዕይታ ጥበብ ከሌሎች የት/ት አይነቶችጋር ያለው ጥምርታ

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የዕይታ ጥበብ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ጥምርታ ያደብራሉ፡፡
- የዕይታ ጥበብ የቋንቋ ትምህርት ጋር ተዋህዶ ፊደላትነ በቀላሉ ይለያሉ፡፡
- የዕይታ ጥበብ የማስላት፣ የማገናዘብ፣ የመሳተፍ፣ ፍላጎታቸውን ይጨምራሉ፡፡
- የእይታ ጥበብን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ጥምርታ ለየትምህርት ውጤታማነትን ያውቃሉ፡፡

### 5.2.4.1 የእይታ ጥበብ ከቋንቋ ጋር ያልው ጥምረት

የዕይታ ጥበብ ትምህርት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር አዋህዶ በማስማማት ቢማሩ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱት የሚረዳ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ በየትምህርት አይነት ጣልቃ መግባት ማለት የዕይታ-ጥበብን ከተለያዩ የሥርዓተ ትምህርት ጋር በማዋሃድ የመማር ማስተማር ሂደቱን አስደሳችና ቀላል ያደርገዋል፡፡ የትምህርቱን ጭብጦች፣የርዕሰ ጉዳዩዮች በፕሮጀክት ሲጣመሩ፣ተማሪዎች በትምህርቶቹ መካከል የመነቃቃት በቀላሉ ነገሮችን የማገናዘብ አቅም ያደብራሉ ፡፡እንደ ቋንቋዎች፣ማህበራዊ ጥናቶች፣ሳይንስ እና ሂሳብ ያሉ ትምህርቶች በክውናና ዕይታ ጥበብ ጋር እንዲገናኙ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የዕይታ-ጥበባት የተለያዩ የትምህርት ርዕሰ-ጉዳዮችን በጣም በቀላል ሁኔታ ያብራራሉ፡፡



ሥዕል፡-የዕ.ጥ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያልው ጥምርታ

## ከተለያዩ ትምህርት ርዕሶች ርዕሰ ጉዳይ ጋር ጥምርታ

ከክወናና ዕይታ-ጥበባት ጋር በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች ማለትም እንደ መመልከትን፣ማሰብን፣መሞከርን፣ማሰስን፣እንደገና መፍጠርን እና መወሰንን መግለፅን ያደብራሉ:: እነዚህ የዕይታ ጥበብ አካቶ ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዘርፎችን በጥሩ ደረጃ ለመከወን ከሚረዱ የእውቀትና የአእምሮ ንቃትን ያሳድጋሉ::




ሥዕል፡-የዕ.ጥ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያልው ጥምርታ

የእይታ ጥበብ ከቋንቋ ሰዋሰው ክፍል ጋር በቀላሉ ሊዋሃድ ይችላል::
ቋንቋ እይታ ጥበብን በመጠቀም በቋንቋ ትምህርት በየምዕራፉ ወይም በየታሪኩ ውስጥ መምህሩ የዕይታ ጥበብን መጠቀም የተለያዩ ፊደላትን በመፃፍና በመቀባት ቀርፀው በማውጣት ተማሪዎች በቀላሉ ለማስረዳትና ለማሳወቅ ያስችላል:: የክወናና ዕይታ ጥበብ እንደ የትምህርቱ ባህሪ ጣልቃ በማስገባት ምሳሌዎችን ለማሳየት እና የፈጠራን ክህሎትን ተማሪዎች እንዲያዳብሩ ዕይታ ጥበብ በመጠቀም አስተማሪው የተለያዩ ቀለማትንና ቁሳቁሶችን መጠቀም ስለሚያስችል የዕይታጥበብንና ሌሎች የትምህርት ዘርፎችን አጣምረው ማከናወን ይቻላል:: ለተማሪዎች በመምህራን ዕርዳታ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን በመሳል በመቀባት እና በመዳሰስ ማስተማር ይችላሉ::




ሥዕል፡-የዕ.ጥ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያልው ጥምርታ

በዕይታጥበብ አካባቢ ሳይንስን ለማስተማር ጥበብን በማከናወን በቀላሉ መማር ያስችላል:: አንድ ፈጣሪ የጫካ ትዕይንት እና ከሳይንስ ጽንሰ-ሀሳብ ጋር የሚዛመድ ድራማን ይፈጥራል::

### 5.2.4.2 የዕይታጥበብ ከማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ጋር ያለው ጥምረት

በማኅበራዊ ጥናቶች ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በእይታ ጥበባት የተሰሩ የሀገር ቅርሶች፣ ሕንፃዎች፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶች በቤታችሁ በሃይማኖት ቦታዎችና በሙዚየሞች ስለሚገኙ መመልከትና ማጥናት የሀገራችን የአካባቢያችሁን የጥበብ ታሪክና የማህበረሰብ እደገት ለመረዳት ያስችላቸዋል:: በሀገራችን ጥንታዊ የጦር ሜዳ መሳሪያዎች ጦርናጋሻ፣ሳራዴ፣ጎራዴና ሾተል ከአልባሳት ደግሞ ካባ፣ በርኖስ፣ ለምድ፣ እጅ ጠባብ ልዩ ልዩ የአስፋፍ ዘዴ የሚታያቸው ጥንታዊ ሱሪና ቀሚሶች፣ ከእንጨት ከብረታ ብረት፣ ከሸክላ የተሰሩ ቁሳቁሶችና በብራናና በጨርቅ ላይ የተሰሩ የቀለም ቅብ ስዕሎችና የድንጋይ እና የእንጨት ቅርፃ ቅርፆችን በትኩረት በሞት በምታስተውሉ በትጊዜ አብዛኛዎች ከተፈጥሮ ሀብቶች በመጠቀም ዛፎችን ፣ ድንጋዩችን እንስሳትንና አፈሮችን በመጠቀም በሳይንስና በክውና ዕይታ ጥበባትን አጣምረው በመጠቀማቸው ዛሬም ድረስ ስራዎቻቸው ዘመናትን ተሻግረው እናያቸዋለን ይህም ሀገር በቀል እውቀቶች የሚታይባቸው ንድፍ ኪነ ህንፃዎች ላይ ሀረጎችና ልዩ ልዩ ቅርፃቅርፆች አርፈውባቸው ለእይታው እና ማራኪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል::ይህንን አብነት አድርገን ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ የከውናና ዕይታ ጥበባትን በመጠቀም ተማሪዎችን በመንካት ፣ በመዳሰስና በመከወን በምናስተምርበት ጊዜ በቀለሉ ማስረዳትና የሚጠበቀውን ውጤት ተማሪዎች ላይ ማየት እንችላለን:: ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ከሥነ -ጥበብ ወይም ከእይታ ጥበብ ጋር በቀላሉ ሊዋሃዱ ይችላሉ::



ሥዕል ፡-የዕ.ጥ ከማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ጋር ጥምርታ

### 5.2.4.3 የዕይታ- ጥበብ ከሂሳብ ጋር ያለው ጥምርታ

ለተማሪዎች የሂሳብ ትምርትን እንደ ወረደ በስሌትና ስሌት ብቻ ለማስተማር መጣር የመማርማስተማር ሂደቱን አሰልቺ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተሻለ ሁነታ ዕይታ ጥበብን አካተን አሳታፊ በሆነ መልኩ ቁጥሮችንና የስሌት ምልክቶችን ቀለም በመቀባት የተለያዩ ቁሶች በመቅረፅ በማተም ተማሪዎች አካላዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ እየተዝናኑ እየቀነሱ እየደመሩ እየከፋፈሉ በቀላሉ የስሌት አይነቶችን እዲለዩ ያስችላል፡፡




ሥዕል፡- የዕይታ-ጥበብ ከሂሳብ ጋር ያልው ጥምርታ

## የምዕራ ማጠቃልያ

ሙዚቃ ት/ት ለህብረተሰብ እጅግ አስፈላጊና ጠቀሜታቸው የጎሉ አካባቢን መንከባከብ ለጤና ጠንቅ የሆኑትን የድምፅ፤የአየር ወዘተ ብክለቶችን ከማሳወቅ ባሻገር ተማሪዎች ትምህርታቸውን በቀላሉ እንዲረዱ ከማስቻል ባለፈ ከብዙ ዕውቀቶች ጋር ቁርኝት አለው ። ውዝዋዜ ሁለንተናዊ የሆነ በማህበራዊ በሳይንሳዊ እውቀቶችን በእንቅስቃሴ እንድናውቅ የሚያሥችል ጥበባዊ ጥንቅር ውጤት ነው።

ለትግበራ የቀረበው አጭር ተውኔት ችግኝ መትከል ለሀገር የሚሰጠውን ጠቀሜታና ሀገር ከምንም በላይ መሆኗን ለማሳየት የተፃፈ ሲሆን ከአሁን በፊት የተማራችኋቸውን ትምህርቶች በማቀናጀት በተግባር በመከወን የምታሳዩበትና ስለሀገራችሁ አውቃችሁ ንቃተ ህሌናችሁን እንድታዳብሩ ታስቦ ነው።

የክወናና ዕይታጥባባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ዝምድና ዘርፍ ብዙ መሆኑን ተገነዘባችሁ አደል ። የዕይታጥበብ ሁሉንም የምህርትት አይነት አጋዥና በቀላሉ ምሳሌዎች ሊሆን በሚያስችል መልኩ መጠቀም ያስችላሉ ። ይህም ማለት ለያንዳንዱ ትምህርት አይነት የከወናና ዕይታ ጥበባት መግባቢያ ቋንቋ መሆን ይችላሉ። በስሻል ትምህርት ብንመለከት ማህበረሰቡ ቤትንና የቤት ውስጥ መገልገያውን መመገቢያውን ሁሉ ጨምሮ የሚሰራቸው፣ የሚያዘጋጃቸው ጥበባዊ በሆነ መልኩ የተፈጥሮን ሀብትን በመጠቀም ነው። ለዚህም በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ጥበበኛ ሰዎች ባለሙያተኞች ይገኛሉ። ተማሪዎች እስቲ በየአከባቢያችሁ የሚገኙ የተለያዩ ሙያ ባለቤቶችን ተመልክታችሁ በምን በምን የጥበብ ዘርፎች ላይ እደንተሰማሩ ለመምህራችሁናለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ትክክል የሆነውን “እውነት” ስህተት የሆነውን “ሀሰት” በማለት መልሱ

1. የክውናና ዕይታጥበብ የማይነካው የትምህርት አይነት የለም።
2. የቤት ቁሳቁሶች ከተፈጥሮን በመጠቀም በጥበብ ባለሙያዎች ነው የሚሰሩት።
3. የክወናና ዕይታ ጥበባት ለትምህርት ስርዓት አጋዥ አይደሉም።
4. ሙዚቃ አለም አቀፍ ቋንቋ እነዲሆን ያስቻሉት ሁለገብ መሆን መቻሉ ነው።
5. ስሜትን ይሰጣል ስንል በተገደበ መልኩ ብቻ ነው።
6. ሃይል ያለው መልህቅ ስንል ለትምህርቶች ማቆሚያ መሰረትማለታችን ነው።
7. ማንኛውም እንቅስቃሴ ስልተ ምት ነው።
8. የድምፅ ብክለት በዋነኝነት የሚያጠቃው የጆሮ ክፍልን ነው።

## ዋቢ መጽሐፍት

-Basic Music Theory: How to read write and understand written music/ Jonathan harnum
-The complet idiotis guide to Music theory / Michael miller
-The College Board: Music Theory course
-Music Theory Fundamentals High-Yield Music Theory, vol. 1 Mark Feezell Learn MusicTheory.net
-መሰረታዊ የውዝዋዜ ፅንሰ ሃሳብ ተመስገን ገብሬ። የጉለሌው ሰካራም።
-ታቦር ገ/መድህን። ስብራትና ሌሎችም። አዲስ አበባ፤ 1998 ዓ.ም።
-ዘሪሁን አስፋው። የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን። አዲስ አበባ፣ ንግድ ባተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።
-ጳውሎስ አእምሮ። የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2010 ዓ.ም።
-ፋንታሁን እንግዳ። የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ። አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም።
-ሰለሞን ኃይለ ማርያም። በስብስብ ላይ የተጻፉ ክረቶችን መለየት(ያልታተመ)።
-Solomon Haile Mariyam. staff, ledger lines, and clefs/August 2020.
-Todd Debrecen. Special make up effects for stage and screen, Making and applying prosthetics. Focal Elsevier press,2009.
-VISUAL AND PERFORING ARTS JUNIOR (GRADE 3-7) SYLLABUS 2015-2022
- Art today
- understanding art
- Teaching Art to young children 2002 Rout ledge Falmer
- Foundation of Art and Design 2008
- Art Education 1996

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓም/2021